በኢትዮጵያ ንግድና
የዘርፍ ማኅበራት
ምክር ቤት

ኢትዮ ቻምበር

ሚዲያ ጭማቂ

በኢትዮጵያ የንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት የኮሚኒኬሽንና ህዝብ ግንኙኙነት መምሪያ የሚዘጋጅ ወርሃዊ የሚድያ ጭማቂ

ጥር 2014 ዓ.ም.

የካፒታል ገበያ ለማስጀመር…2

ቻይና ከኢትዮጵያ የምታስገባው…2

ኢትዮጵያ ከአጎዋ በመሰረዟ…2

ያለማስያዣ ብድር…2

ከሐምሌ ወር ጀምሮ… 3

በከፍተኛ ሁኔታ ተጎድቶ…3

ወደ ውጭ የሚላኩ የጥራጥሬና…3

የኢትዮጵያ አየር መንገድ…3

ኢትዮጵያ፣ ጅቡቲ እና ሩሲያ…4

የግብርና ዘርፍ የወጪ…4

የጥጥ ዋጋ ከሦስት…5

በግንባታ ዘርፍ የሚያጋጥሙ…5

ዳያስፖራዎች በኢንቨስትመንት ጉዳይ…5

ባንኮች የደንበኞቻቸውን ዝርዝር…6

ታሪካዊ የተባለው የቡና…7

የኢትዮጵያ ንግድ ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት በአማራ እና አፋር ክልል ለሚገኙ ተፈናቃዮች ድጋፍ አደረገ

የኢትዮጵያ ንግድ ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት፤ የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስትር እና የተጠሪ ተቋማቱ እንዲሁም የኢትዮጵያ ሲሚንቶ አከፋፋዮች ማኅበር በአማራ እና አፋር ክልል ለሚገኙ ተፈናቃዮች የገንዘብ እና የዓይነት ድጋፍ አደረጉ።

በክልሉ ተገኝተው ድጋፉን ያስረከቡት የንግድ ሚኒስትሩ አቶ መላኩ አለበል፣ የምክር ቤቱ ፕሬዚደንት ኢኒጂነር መላኩ እዘዘው እና ሌሎች ከፍተኛ ኃላፊዎች ናቸው።

ተቋማቱ አሸባሪው የትግራይ ወራሪ ቡድን በወረራ ይዟቸው በነበሩት አካባቢዎች የተፈናቀሉ ወገኖችን መልሶ ለማቋቋምና የወደሙ ተቋማትን መልሶ ለመገንባት እንዲቻል 10 ሚሊዮን ብር በጥሬ ገንዘብና 4 ሚሊዮን ብር በዓይነት አስረክበዋል።

አሁናዊ ችግሮችን መሻገር የምንችለው አብሮ በመቆም ፤ አንዱ ለሌላው ደራሽ በመሆንና በመተሳሰብ ነው ያሉት የኢትዮጵያ ንግድ ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚደንት ኢኒጂነር መላኩ እዘዘው ምክር ቤቱ ያደረገው ይህ ድጋፍ በቀጣይ ተጠናክሮ እንደሚቀጥልም አረጋግጠዋል ። የተደረገው ድጋፍ ከሰራተኞች እና ከምክር ቤቱ የተገኘ መሆኑን የገለጹት ፕሬዝዳንቱ በዚሁ አጋጣሚ የምክር ቤቱ ሰራተኞች ላደረጉት ድጋፍ ምስጋናቸውን አቅርበዋል።

በተጨማሪም የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር እና የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር፣ ከተጠሪ ተቋማት እንዲሁም ከኢትዮጵያ ሲሚንቶ አከፋፋዮች ማኅበር ጋር በመሆን በአሸባሪው ሕወሓት ወረራ እና ጥቃት ለተፈናቀሉ የአፋር ክልል ወገኖችም ድጋፍ አድረጓል።

የሩሲያ ልዑካን ቡድን ጉብኝት

የኢትዮጵያ የንግድ እና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ም/ዋና ፀኃፊ አቶ ውቤ መንግስቱ በሩሲያ ፌዴሬሽን የአፍሪካ አገራት የኢኮኖሚ ትብብር ማስተባበሪያ ኮሚቴ(The Coordination Committee on Economic Cooperation with African Countries) ስራ አስፈጻሚ ዶክተር ሰታኒስለቭ ሜሴንቴሴቭ የተመራ የልዑካን ቡድንን ተቀብለው በተለያዩ የኢንቨስትመንት እና ንግድ ጉዳዮች ዙሪያ ውይይት አደረጉ።

ስራ አስፈጻሚ ዶክተር ሰታኒስለቭ ሜሴንቴሴቭ በውይይቱ ላይ እንደተናገሩት የሩሲያ ፌዴሬሽን በኢትዮጵያ የንግድ እና የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ውስጥ ያለውን ተሳትፎ ማሳደግ በመፈለጉ ለዚህም ይረዳ ዘንድ በአገሪቱ ያሉ አማራጮችን በማጥናት ላይ ይገኛል ።

የሁለቱ አገራት ካላቸው ታሪካዊ ግንኙነት አንጻር የንግድና ኢንቨስትመንት ትስስሩ የሚጠበቀው ደረጃ ያለመሆኑንም ያነሱት ዶክተር ሰታኒስለቭ ፤ ትስስሩን ለማጠናከር የሚያግዙ የኦነላይን ቢዝነስ ፎረም እና በሩሲያ የሚካሄድ የንግድ ውይይት መድረክ እና ኤግዚቢሽን በቅርቡ ለማካሄድ ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን ገልጸዋል። የኢትጵያ ንግዱ ዘርፍ ተሳትፎ እንዲያደርግ የምክር ቤቱን ትብብርም ጠይቀዋል።

|የኢትዮጵያ የንግድ እና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ም/ዋና ፀኃፊ አቶ ውቤ መንግስቱ በበኩላቸው በሁለቱ አገራት መካከል ያለውን የንግድ እና ኢንቨስትመንት ትስስር ለማሳደግ ምክር ቤቱ የተቻለውን ሁሉ እንደሚያደርግ ገልጸው፤ በቅርቡ ለሚካሄዱት የቢዝነስ ፎረም እና ኤግዚቢሽን የግሉዘርፍ ተሳትፎ እንዲያደርግ እና ከሩሲያ አቻዎቹ ጋር በጋራ ሊሰሩ በሚችሉ ተግባራት ዙሪያ ምክክር እንዲያደርግ ለማስቻል እንደሚሰራ ተናግረዋል።

የካፒታል ገበያ ለማስጀመር የተቋቋመው ፕሮጀክት ቴክኒካዊ ሥራዎችን እየጨረሰኩ ነው አለ

የኢትዮጵያ ካፒታል ገበያን ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን እ.ኤ.አ. በ2022 ሥራ ለማስጀመር በብሔራዊ ባንክ የተቋቋመው ፕሮጀክት፣ ቅድመ ቴክኒካዊ ሥራዎችን እንያገባደደ መሆኑ ተገለጸ፡፡

አዳዲስ የፈጠራ ሥራዎችን ከፋይናንስ ምንጮች ጋር በማገናኘት ኢንቨስትመንትን ለማበረታት፣ ኢንቨስተሮችን ለመጠበቅ፣ ገበያውን ፍትሐዊ፣ ተዓማኒና ቀልጣፋ በማድረግ፣ በአገሪቱ የፋይናንስ ሥርዓት ላይ የሚፈጠሩ መዋቅራዊ ሥጋቶችን ለመለየት፣ ለመከላከልና ለመቀነስ ያስችላል የተባለለት የካፒታል ገበያ ባለሥልጣንን የሚያቋቁመው አዋጅ፣ በሰኔ 2013 ዓ.ም. በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ፀድቆ ወደ ሥራ መግባቱ ይታወሳል፡፡

አዋጁ ከፀደቀ ጀምሮ ተቆጣጣሪ ባሥልጣኑን ለማቋቋም የሚያስችሉ ቴክኒካዊ ሥራዎችን ለማከናወን በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን የተካተቱበት 13 የባለሙያዎች ቡድን ተዋቅሮ፣ ሥራውን የሚፈጽም ፕሮጀክት ተቋቁሞ መመርያ በማውጣት፣ እንዲሁም እንግሊዝ አገር ከሚገኘው ስታንዳርድ ባንክ ጋር በመተባበር የአቅም ግባታ ሥራዎችን በማከናወን ላይ እንደሚገኝ በብሔራዊ ባንክ የካፒታል ገበያ ከፍተኛ አማካሪ አቶ መለሰ ምናለ ለሪፖርተር ተናግረዋል፡፡

በተጨማሪም የውጭ ኢንቨስትመንት ባንኮች ወደ ኢትዮጵያ መጥተው በተለይም የካፒታል ገበያ አክሲዮን ማሻሻጥ፣ የቦንድ ዲዛይን መሥራት፣ የኢንቨስትመንት ምክር አገልግሎትና መሰል የካፒታል ገበያ ኢንቨስትመንት ላይ እንዲሰማሩ ሕጉ የሚፈቅድ በመሆኑ፣ በቅርቡ የውጭ ኢንቨስትመንት ባንኮች ፍጎታቸውን ሊገልጹ እንደሚችሉ በመግለጽ፣ ለአብነትም ስታንዳርድ ባንክ በኢትዮጵያ ላሉ ባለሙያዎች በነፃ ሥልጠና መስጠት መጀመሩ አንዱ የፍላጎት ማሳያ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል ብለዋል፡፡

የመንግሥት የኢኮኖሚክ ሪፎረም አካል የሆነው የካፒታል ገበያ መመሥረት የአጠቃላይ የኢኮኖሚውን ሚዛን ለመጠበቅና ምርታማነትን ለመጨመር ትልቅ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው የገለጹት አቶ መለሰ፣ ከሚቋቋመው ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ጋር አብረው ይሠራሉ ለሚባሉ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ሥልጠናና ማረጋገጫ (Certification) እየተሰጠ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የንግድ ሥራ ትምህርት ቤት የአካውንቲንግና የፋይናንስ ትምህርት ክፍል ኃላፊ ዳኪቶ ዓለሙ (ዶ/ር) ለሪፖርተር እንደገለጹት፣ ምንም እንኳ የካፒታል ገበያም ሆነ የፋይናንስ ተቋማት ገንዘብ ያለውና የሌለው ሰው አንድ ላይ የሚገናኙባቸው መድረኮች ቢሆኑም፣ አሁን ካለው አሠራር በተለየ የካፒታል ገበያ መምጣት የፈጠራ ሥራዎች የበለጠ እንዲደገፉና

◈

ቻይና ከኢትዮጵያ የምታስገባው የቡና ምርት መጠን ማደጉ ተገለፀ

ቻይና ከኢትዮጵያ የምታስገባው የቡና ምርት መጠን በ196 በመቶ አደገ፡፡

ጥር 12፣ 2014 ዓ.ም በቻይና የኢትዮጵያ አምባሳደር ተሾመ ቶጋ የተሳተፉበት ሰሚናር ተካሂዷል፡፡

ሰሚናሩ በዋናነት ባለፈው የፈረንጆቹ ዓመት የተካሄደው የቻይና-አፍሪካ የትብብር ፎረም ውሳኔዎች አፈፃፀምን መከታተል ዓላማ ያደረገ ነበር፡፡

በዚህ ኩነት ላይ ብቻ በአምስት ሰከንድ ውስጥ 11 ሺህ የኢትዮጵያ ቡና እሽጎች መሸጣቸውን ነው በቻይና የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የአፍሪካ ጉዳዮች ዋና ዳይሬክተር ዉ ፔንግ ያስታወቁት፡፡

በፈረንጆቹ 2021 ዓመተ ምህረት ላይ ቻይና ከኢትዮጵያ ያስገባቸው የቡና ምርት መጠን ከቀደመው ዓመት በ196 በመቶ ማደጉን የገለፁት ዋና ዳይሬክተሩ፥ በሚቀጥሉት ዓመታት ቻይና መጠኑ ከፍ ያለ የግብርና ምርት ከአፍሪካ ሀገራት ታስገባለች ብለዋል፡፡

◈

ለተጨማሪ መረጃ፡

https://www.fanabc.com/ቻይና-ከኢትዮጵያ-የምታስገባው-የቡና-ምር/

ኢትዮጵያ ከአጎዋ በመሰረዟ 64 በመቶ የሚሆኑ የቆዳ ውጤቶችን ለመላክ መቸገሩን መንግሥት አስታወቀ

እ.ኤ.አ. ጃንዋሪ 1 ቀን 2022 ጀምሮ ተፈጻሚ መሆን የጀመረው ኢትዮጵያ ከአሜሪካ መንግሥት ታገኘው የነበረው ከኮታና ከቀረጥ ነፃ የንግድ ዕድል (አጎዋ) መሰረዝ ውሳኔ፣ 64 በመቶ የሚሆኑ የቆዳ ውጤቶችን ወደ ውጭ ለመላክ ‹‹አስቸጋሪ›› ሁኔታ መፍጠሩን የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

የኢንዱስትሪ ሚኒስትሩ አቶ መላኩ አለበል ቀደም ሲል ለዲያስፖራዎች በተዘጋጀ የኢንቨስትመንት ፎረም ላይ ተገኝተው በዘርፉ ያሉ የኢንቨስትመንት አማራጮችን ባቀረቡበት ወቅት የአሜሪካ፣ የካናዳና የአውሮፓ ገበያዎችን የሸፈኑ የቆዳ ምርቶች ኢትዮጵያ ውስጥ እየተመረቱ መሆኑን ተናግረው ነበር፡፡ ‹‹አሁን በአጎዋ ምክንያት 64 በመቶ የሚሆኑ ቆዳና የቆዳ ውጤቶች ወደ አሜሪካ ለመላክ እየተቸገርን ነው፤›› ብለዋል፡፡

ኢትዮጵያ ላለፉት 21 ዓመታት አጎዋን ተጠቅማ በተለይ የጨርቃ ጨርቅ ውጤቶችን ወደ አሜሪካ ከቀረጥ ነፃ ስትክል የቆየች ሲሆን፣ ኢትዮጵያ ውስጥ ከሚመረቱ ጫማዎችና የቆዳ ውጤቶች ውስጥ 78 በመቶ የሚሆነው መዳረሻው አሜሪካ ነበር፡፡

የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር አቶ ዳኛቸው ሽፈራው ወደ አሜሪካ የሚላኩት እንደ ጫማ፣ ቦርሳና አልባሳት ያሉና የፋሽን ምርት የሆኑ የቆዳ ውጤቶች መሆናቸውን ተናግረዋል፡፡ እነዚህ ምርቶች በትልልቅ፣ በመካከለኛና በትንንሽ ኢንዱስትሪዎች እንደሚመረቱ የተናገሩት ዋና ዳይሬክተሩ፣ የአጎዋን ተጠቃሚነት መሠረት በማድረግ የተቋቋሙ ፋብሪካዎች እንዳሉ አስረድተዋል፡፡

ዳይሬክተሩ፣ ‹‹ኒው ዊንግ›› የተሰኘውን የጫማ አምራች ፋብሪካና ‹‹ሄጅ ዋን›› የተባለውን ከስምንት ሺሕ በላይ ሠራተኞች ያሉት ፋብሪካ እንደሆነ የጠቀሱ ሲሆን፣ እነዚህ ፋብሪካዎች ቀጥታ ገበያቸው አሜሪካ መሆኑንና የቀረጥ ነፃ ጥቅም ላይ መሠረት ያደረጉ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ከ40 በላይ መካከለኛና አነስተኛ ኢንዱስትሪዎች እንዳሉ የገለጹት አቶ ዳኛቸው፣ ኢትዮጵያ ከአጎዋ ተጠቃሚነት በመሰረዟ ምክንያት ሠራተኛና ምርት የሚቀንሱ ፋብሪካዎች እንደሚኖሩ አስታውቀዋል፡፡ ከዚህም ባሻገር ‹‹ከእነ አካቴው ሊበተኑ የሚችሉ ፋብሪካዎች እንደሚኖሩ ጥናቶች ያሳያሉ፤›› ብለዋል፡፡

እነዚህ ፋብሪካዎች የሚያመርቷቸው የፋሽን የቆዳ ውጤቶች ተጠቃሚዎች ያሉት አሜሪካ ውስጥ እንደሆነ ጠቁመው፣ አብዛኛው የውጭ ምንዛሪ የሚገኘው ከዚህ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡ ያለቀለት ቆዳ የሚላከው ወደ አውሮፓና እስያ መሆኑ ታውቋል፡፡

በዚህም ሳቢያ ፋብሪካዎቹ ወደ ውጭ መላክ እንዳያቆሙ አማራጭ እየተፈለገ መሆኑን ያስረዱት አቶ ዳኛቸው፣ ‹‹ቀረጥ ቢጣልባቸውም ትርፋቸው ይቀንሳል እንጂ ገበያቸው አይጠፋም፤›› ብለዋል፡፡ ይሁንና ትርፋቸው በመቀነሱ ለጉዳት እንዳይዳረጉ የማምረቻ ዋጋቸውን ቀንሰው እንዲያመርቱ ሥልጠና ለመስጠት፣ መንግሥትም በማበረታቻ የማምረቻ ወጪያቸውን ሊቀንስ

◈

ያለማስያዣ ብድር መጀመሩ ተገለፀ

በኢትዮጵያ የባንክ ኢንዱስትሪ ውስጥ ያለ ማስያዣ ብድር አይታሰብም፡፡ ለየትኛውም የብድር ዓይነት ባንኮች ንብረት ሳይዙ ብድር አይሰጡም፡፡ አዋጭ ሊሆን ይችላሉ ለተባሉ ፕሮጀክቶች ሳይቀር ፋይናንስ ለማግኘት ማስያዣ ከሌለ አይሞከርም፡፡ ብድር በቀላሉ አለማግኘት ዋናው ችግርም ነው፡፡

በአገሪቱ ባንኮች የሚጠቀሙ ተበዳሪዎች ቁጥር በእጅጉ አነስተኛ ሆኖ ለመገኘቱ አንዱ ምክንያት ተደርጎ የሚወሰደው ይኼው ያለ ማስያዥ ብድር መስጠት የማይቻል ከመሆኑ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ በኢትዮጵያ ከ66 ሚሊዮን በላይ አካውንት የከፈቱ የባንክ ደንበኞችና ወደ 1.5 ትሪሊዮን ብር የሚደርስ ተቀማጭ ገንዘብ ያሰባሰቡ የኢትዮጵያ ባንኮች ባሉበት የተበዳሪዎች ቁጥር ሲታይ እዚህ ግባ አይባልም፡፡

በ2013 የሒሳብ ዓመት ባንኮች የሰጡት ብድር አንድ ቢሊዮን እንኳን የማይደርስ ነው፡፡ ከዚህ ውስጥ አብዛኛው በተደጋጋሚ ብድር የሚወሰድ ሲሆን፣ በየዓመቱ ይጨምራል ተብሎ የሚታሰበው አዲስ ተበዳሪ ቁጥር አነስተኛ ስለመሆኑ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ ለዚህም እንደ አንድ ምክንያት ሊጠቀስ የሚችለው በተለይ ለአነስተኛና መካከለኛ ቢዝነሶች ባንኮች የሚሰጡት ብድር ኢምንት የሚባል መሆኑ ነው፡፡

የኦሮሚያ የኅብረት ሥራ ባንክ ፕሬዚዳንት አቶ ደርቤ አስፋው እንደሚገልጹትም፣ ባንኮቹ ለአነስተኛ መካከለኛ ቢዝነሶች፣ እንዲሁም ለአርሶ አደሮች የሚቀርብ ብድር አለ ማለት የማይቻል መሆኑን ነው፡፡

ከሐምሌ ወር ጀምሮ የንግድ ፈቃድ ማውጣት የሚቻለው በበይነ መረብ ብቻ መሆኑ ተገለጸ

ከሐምሌ ወር 2014 ዓ.ም. ጀምሮ የንግድ ፈቃድ ማውጣት የሚቻለው በበይነ መረብ ብቻ መሆኑን፣ የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር አስታወቀ።

ባለፈው ዓመት ጥር ወር የተጀመረው በበይነ መረብ የንግድ ፈቃድና ምዝገባ የመስጠት አገልግሎት፣ ኅብረተሰቡ በታሰበው ልክ እየተጠቀመበት እንዳልሆነ፣ በንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር የንግድ ምዝገባና ፈቃድ ደንበኞች አገልግሎት ዳይሬክተር አቶ ጅራታ ነመራ ገልጸዋል።

የንግድ ሥርዓቱን ቀላል ለማድረግ ከተወሰዱ ዕርምጃዎች መካከል አገልግሎቶችን በበይነ መረብ ማድረግ አንዱ መሆኑን የጠቀሱት አቶ ጅራታ፣ ለዚህም ከሐምሌ ወር ጀምሮ ንግድ ቢሮዎች በአካል በመገኘት የሚደረገው ምዝገባና የፈቃድ አሰጣጥ ሙሉ ለሙሉ ይቀራል ብለዋል።

አሠራሩ የንግድ ፈቃድ ለማውጣት የሚወስደውን ጊዜና ገንዘብ ከመቀነስ ባለፈ መደበኛ የንግድ ሥራን ለማበረታታት፣ ሙስናን ለመከላከል፣ በንግድና ኢንቨስትመንት የኢትዮጵያን ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነት ለማሳደግ ያስችላል ሲሉ አስረድተዋል።

የንግድ ፈቃድና ምዝገባውን ለማድረግ ከዚህ በፊት ሲጠየቅ የነበረው የቤት ኪራይ ውልም የማያስፈልግ በመሆኑ፣ ተገልጋዮች በቀላሉ መመዝገብና ፈቃድ መውሰድ ይችላሉ ብለዋል።

በኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ጽሕፈት ቤት ዳይሬክተር አብዮት ባዩ (ዶ/ር) በበኩላቸው፣ በበይነ መረብ ንግድ የሚያከናውኑ አካላትን ለመቆጣጠር የሚያስችል መመርያ ተዘጋጅቶ ለፍትሕ

በከፍተኛ ሁኔታ ተጎድቶ የነበረው የሆቴሎች ገበያ መነቃቃት እያሳየ ነው

በጠቅላይ ሚኒስትር ዓብይ አህመድ (ዶ/ር) ጥሪ መሠረት ዳያስፖራዎች ወደ አገር ቤት ሲመጡ፣ በተለይ በአገልግሎት ዘርፉ ላይ መነቃቃት እንደሚፈጥር ሆቴሎች ተስፋ አድርገው ነበር። ከእንግዶቹ መምጣት ጋር ተያይዞም በአዲስ አበባና በመላ አገሪቱ የሚገኙ ሆቴሎች፣ በአገልግሎት ዋጋቸው ላይ የ30 በመቶ ቅናሽ በማድረግና አዳዲስ ሁነቶችን በማዘጋጀት ጎብኝዎቻቸው ለመሳብ መሞከራቸውን ይገልጻሉ።

የጎልደን ቱሊፕ ሆቴል ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ደረጀ ቦጋለ የሆቴሉ የክፍሎች የመያዝ ምጣኔ (Occupancy Rate) ከሃያ በመቶ በታች እንደነበር ገልጸው፣ በአሁኑ ወቅት ግን በዳያስፖራዎች መምጣት ምክንያት ቁጥሩ ወደ 40 በመቶ ከፍ ማለቱን አስረድተዋል።

የዳያስፖራዎች መምጣት በገበያው ላይ ካደረገው ቀጥተኛ አስተዋጽኦ በተጨማሪ፣ ከውጭ አገር በሚመጡ የሌላ አገር ዜጎችም ዘንድ የነበረው እምነት እንዲጨምር፣ በሌሎች ደንበኞች ቁጥር ላይም ከፍተኛ ለውጥ እንዲመጣ ማድረጉን አቶ ደረጀ ገልጸዋል።

ላለፉት ሃያ ዓመታት በአገልግሎት ዘርፉ ላይ የቆየው ኩሪፍቱ ሪዞርት በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል ጦርነት፣ እንዲሁም በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ምክንያት ከፍተኛ የገበያ ዕጦት ካጋጠማቸው መካከል አንዱ ነበር። በጦርነቱ ምክንያት አንዳንድ ቅርንጫፎቹ ሙሉ ለሙሉ ተዘግተው እንደነበር የድርጅቱ የማርኬቲንግ ኃላፊ አቶ ሚካኤል ተስፋዬ ገልጸዋል።

ነገር ግን ዳያስፖራዎች ከመጡ በኋላ የደንበኞች ቁጥር በእጥፍ መጨመሩን አስረድተዋል። ‹‹በኮቪድ-19 እና በሰሜናዊው የኢትዮጵያ ክፍል ጦርነት፣ በሁሉም ቅርንጫፎቻችን ላይ ከፍተኛ የገበያ ውድቀት ነበረ፣ አሁን ግን መሻሻል እየታየ ነው፤›› ብለዋል።

‹‹የአገር ውስጥ ደንበኞቻችን ቁጥር መቀነስ ምክንያት ጦርነቱና የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ቢሆኑም፣ በአሁኑ ወቅት የዳያስፖራዎች መምጣት በራስ መተማመንን በማሳደጉ የአገር ውስጥ ደንበኞቻችን ቁጥር እየጨመረ ነው፤›› ሲሉም አክለዋል።

የዳያስፖራው መምጣት ሆቴሎችን በገበያ ብቻ ሳይሆን በአስተሳሰብም አነቃቅቷቸዋል የሚሉት የኦዚ የሆቴልና ማኔጅመንት አማካሪ ማኔጂንግ ዳይሬክተር አቶ ቁምነገር ተከተል፣ የአገልግሎት አሰጣጣቸው ላይም መሻሻል መታየቱን ገልጸዋል።

ወደ ውጭ የሚላኩ የጥራጥሬና የቅባት እህሎች ዋጋ ማሻቀብ ዋነኛ ገዥ አገሮችን እያሸሸ ነው ተባለ

በኢትዮጵያ በስፋት የሚመረቱት የጥራጥሬና የቅባት እህሎች ዋጋ በዓለም አቀፍ ገበያ ከፍ ማለት ዋነኛ ገዥ አገሮችን እያሸሸ እንደሆነ ተገለጸ። ይህ የተገለጸው የኢትዮጵያ ጥራጥሬ፣ ቅባት እህሎችና ቅመማ ቅመም አዘጋጅቶ ላኪዎች ማኅበር 10ኛውን የቅባትና ጥራጥሬ ዓለም አቀፍ ኮንፍረንስ በበይነ መረብ አማካይነት፣ ጥር 5 ቀን 2014 ዓ.ም. በአዲሱ ኢሊሌ ሆቴል ባከናወነበት ወቅት ነው።

በውይይቱ ከ20 አገሮች ማለትም ከአፍሪካ፣ ከአውሮፓ፣ ከሰሜን አሜሪካና ከእስያ አገሮች የተወጣጡ ከ102 በላይ የዘርፉ ተሳታፊዎች በበይነ መረብ የተካፈሉ ሲሆን፣ በኮንፍረንሱ ላይ ዓለም አቀፍና አገር ዓቀፍ የጥራጥሬና ቅባት እህሎች ከምርት አንስቶ እስከ ግብይት ያለው አሠራር ምን ይመስላል? የሚለውን ጉዳይ የሚያስረዱ ጥናቶች ቀርበውበታል።

ለአብነትም ዋይኤችኢኤንዩ (YHAENU) ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል አስመጪና ላኪ ድርጅት ኃላፊ የሆነት አቶ ሳሙኤል መልኬ ባቀረቡት ጥናት እንዳስታወቁት፣ ኢትዮጵያ ቁጥራቸው ቀላል የማይባሉ የጥራጥሬ ምርቶችን ወደ የተለያዩ አገሮች ትልካለች። ባለፉት አምስት ዓመታት አገሪቱ ሦስት ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን የሚጠጋ የጥራጥሬ ምርቶችን እንደላከች ተገልጿል። ወደ ውጭ የሚላከው የምርቶች መጠን በተለይም በ2010 ዓ.ም. ከፍተኛ እንደነበር አስረድተው፣ ቀጥሎ ባሉት ዓመታት እያሽቆለቆለ እንደመጣ ለዚህም ዋነኛው ምክንያቶቹ በሕገወጥ መንገድ ወደ ኬንያና ሌሎች አገሮች የሚደረገው ሕገወጥ ንግድ አንዱ ተጠቃሽ ምክንያት እንደሆነ ገልጸዋል።

ላለፉት አምስት ተከታታይ ዓመታት 1.8 ሜትሪክ ቶን የጥራጥሬ ምርቶችን ኢትዮጵያ ወደ ውጭ አገሮች የላከች ሲሆን፣ ባለፈው የምርት ዘመን በአጠቃላይ ከተመረተው ምርት አሥር ከመቶው ወደ ውጭ አገሮች ተልኳል።

ምንም እንኳን የተባበሩት ዓረብ ኤምሬትስ፣ የመን፣ ሲንጋፖር የመሳሰሉት የእስያ አገሮች የተለያዩ የጥራጥሬ ምርቶችን የሚገዙበት መጠን ቢጨምርም፣ ነገር ግን በስፋት ምርቱን ከዚህ ቀደም ይገዙ የነበሩ አገሮች ከገዢ ዝርዝር ተሳትፏቸው ራሳቸውን እያገለሉ እንደሚገኙ፣ ከእነዚህም ውስጥ ቱርክ፣ ቬትናም፣ ኢንዶኔዢያ፣ ፓኪስታንና ቻይና ተጠቃሾቹ ናቸው።

እንደ አኩሪ አተር ያሉ ምርቶች ወደ ውጭ አገሮች የሚላኩበት መጠን መቀነሱ በአገር ውስጥ ለምግብ ዘይት አምራች ፋብሪካዎች በጥሬ ዕቃ ግብዓትነት ከመቅረባቸው ጋር የሚያያዝ እንደሆነ አቶ ሳሙኤል ገልጸዋል።

በተለይ የጥራጥሬ ምርቶች ብዙ የንግድ ሰንሰለቶችን አልፈው ኤክስፖርተሩ ጋር የሚደርሱበት ዋጋ ከፍተኛ መሆኑን፣ ምርቱም ከአገር ሲወጣ የሚቆረጥለት ዋጋ ከፍተኛ እንደሆነ፣ በዚህ ምክንያት ገዢዎች ከሌሎች አገሮች የተሻለ ዋጋ ስለሚያገኙ ምርቱን እንዳይገዙ እንደሚያደርጋቸው ተገልጿል። ምርቶቹ ከምርት ገበያ ባለሥልጣን ሲወጡ የሚኖራቸው የጥራት ደረጃ በምርት ገዢ አገሮች ፍላጎት ላይ የራሱ የሆነ አሉታዊ አስተዋፅኦ እንዳለው ተወስቷል።

የኢትዮጵያ ጥራጥሬ፣ ቅባት እህሎችና ቅመማ ቅመም አዘጋጅቶ ላኪዎች ማኅበር ምክትል ፕሬዚዳንት አቶ ኤዳዎ አብዲ በመድረኩ እንደገለጹት፣ እንደ ነጭ ቦሎቄ ያሉት በአውሮፓ አገሮች መዳረሻቸው የነበሩ ምርቶች ኤክስፖርት መቀነሱ ከጥራት ጋር የሚያያዝና መንግሥት በቀጣይ ተግባራዊ በሚያደርገው ረቂቅ ኤክስፖርት ስትራቴጂ እንደሚመለስ እምነታቸው እንደሆነ ገልጸዋል። መንግሥት ከሚከተለው ኢኒሼቲቭ ጋር ተያይዞ ለምግብ ዘይት አገራዊ ምርት ፍጆታ ሲባል ወደ ውጭ የሚላከው አኩሪ አተር እንደቀነሰም ጨምረው አስታውቀዋል።

የኢትዮጵያ የጥራጥሬና ቅባት እህሎች መዳረሻ ከፍተኛ ተቀባይ አገሮች የሆኑት ቱርክና ቻይና ያሉ አገሮችን በጥንቃቄ መያዝ ይገባል ያሉት አቶ ኤዳዎ፣ ከዚህ በሻገርም የኢትዮጵያ የኤክስፖርት ንግድ አሠራር በጥናት ሊደገፍ እንደሚገባውና የሚቆረጠው ዋጋ የዓለም አቀፍን ገበያ መሠረት አድርጎ እንዲቀርብ ለማድረግ ከዘርፍ ማኅበራት አንስቶ፣ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የመንግሥት ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች መሥራት እንዳለባቸው አስታውቀዋል።

ኮንፍረንሱን በይፋ ያስጀመሩት የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስትር ደኤታ አቶ ዳንኤ ቦሩ በበኩላቸው፣ ኢትዮጵያ የጥራጥሬና ቅባት

የኢትዮጵያ አየር መንገድ ቦይንግ 737 ማክስ አውሮፕላኖችን ወደ በረራ ሊያስገባ ነው ተባለ

የኢትዮጵያ አየር መንገድ ቦይንግ 737 ማክስ አውሮፕላኖችን ወደ በረራ ሊያስገባ መሆኑን አስታወቀ።

አየር መንገዱ አውሮፕላኖቹን ለድጋሚ በረራ ዝግጁ ያደረገው ከሚመለከታቸው ዓለም ዐቀፍ የበረራ ተቆጣጣሪዎችና ሌሎች በርካታ የቁጥጥር አካላት የተደረገውን ተደጋጋሚ የደኅንነት ማረጋገጫ ተከትሎ መሆኑንም አስታውቋል።

አየር መንገዱ የቦይንግ 737 ማክስ አውሮፕላኖችን ለበረራ ዝግጁ ያደረገው 36 አየር መንገዶች አውሮፕላኖቹን ለንግድ በረራ መጠቀማቸውንና ደኅንነታቸው የተረጋገጠ መሆኑን ተከትሎ የወሰነው ውሳኔ እንደሆነም ገልጿል።

እንዲሁም 36 አየር መንገዶች ቦይንግ 737 ማክስ አውሮፕላኖችን በመጠቀም ከ3 መቶ 30 ሺሕ በላይ ተጓዦችን ሲያጓጉዙ የደኅንነት ችግር እንዳልገጠማቸው አየር መንገዱ በዋቢነት ጠቅሷል።

ከዚህም በተጨማሪ የአየር መንገዱ አብራሪዎች፣ የበረራ መሃንዲሶች፣ የአውሮፕላን ጥገና ባለሙያዎች እና የመስተንግዶ ባለሙያዎቹ በሙሉ ደኅንነቱ ለተረጋገጠ በረራ ዝግጁ በመሆናቸው የተወሰነ ውሳኔ መሆኑንም ማሳወቁን ከኢዜአ የተገኘው መረጃ ያመለክታል።

ለተጨማሪ መረጃ፡

ኢትዮጵያ፣ ጅቡቲ እና ሩሲያ የጋራ የንግድ ፎረም አካሄዱ

“የኢትዮጵያ፣ የጅቡቲ እና የሩስያ ቢዝነስ ፎረም” በሚል ርዕስ በንግድ ጉዳዮች ላይ የመከረ መድረክ በሞስኮ ተካሄደ።

የአፍሪካ ኢኮኖሚ ትብብር አስተባባሪ ኮሚቴ (AFROCOM) እና የሩሲያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት በመተባበር ያዘጋጁት ይህ የውይይት ፎረም በበይነ መረብ ተካሂዷል።

የኢትዮጵያ እና የጅቡቲ የንግድ ምክር ቤቶች ተወካዮች፣ ሚኒስትሮች፣ በኢትዮጵያ እና ጅቡቲ የሩሲያ ፌዴሬሽን አምባሳደሮች፣ በሩሲያ የኢትዮጵያ አምባሳደር ዓለማየሁ ተገኑ እና የተለያዩ ከፍተኛ የመንግስት የሥራ ኃላፊዎች በፎረሙ ተሳትፈዋል።

በውይይቱ በኢትዮጵያ በኩል የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን፣ የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት እና የኢትዮጵያ ቡና እና ሻይ ማህበር የሥራ ኃላፊዎች ገለጻ አድርገዋል።

ፎረሙ በጥቃቅንና አነስተኛ የሩስያ የንግድ ድርጅቶች ተሞክሮ ላይ ግንዛቤ በመፍጠር ፣ የኢትዮጵያ እና የጅቡቲ የኢንቨስትመንት አቅምን በግልፅ ለማሳየት እንዲሁም የሁለትዮሽ የንግድ እና የኢኮኖሚ ግንኙነትን በማሻሻል ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር ያለመ እንደሆነም ነው የተገለጸው።

ከዚህ በተጨማሪም በአፍሪካ ኢኮኖሚ ትብብር አስተባባሪ ኮሚቴ አዘጋጅነት ወደ ኢትዮጵያ እና ጅቡቲ ለሚደረጉ የንግድ ለውውጥና ትስስር እንደመነሻ እንደሚሆንም ነው የተጠቀሰው።

◆

የግብርና ዘርፍ የወጪ ንግድ አፈፃፀም

ባለፉት 6 ወራት ከግብርናው ዘርፍ የውጪ ንግድ 1 ነጥብ 3 ቢሊየን የአሜሪካ ዶላር መገኘቱን የግብርና ሚኒስተር አስታወቀ:: ይህም አፈፃፀም የዕቅዱ 109 በመቶ መሆኑን ነው ያመለከተው።

ይህ ከባለፈው አመት የ6 ወር አፈፃፀም ጋር ሲነፃፀር የ323 ነጥብ 6 ሚሊየን የአሜሪካ ዶላር፥ ማለትም 32 በመቶ ጭማሪ ማሳየቱ ነው የተገለጸው።

በዚህም ግብርናው ከሀገራዊ አፈፃፀሙ 70 በመቶ ድርሻ እንደነበረው ያመላክታል ነው የተባለው።

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በሂደቱ አስተዋፅኦ ለነበራቸው ሁሉ ምስጋና ያቀረበ ሲሆን፥ በቀጣይ 6 ወራትም ተጠናክሮ እንደቀጥል መጠየቁን ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የማህበራዊ ትስስር ገጽ ያገኘነው መረጃ ያመለክታል።

ለተጨማሪ መረጃ፡

ለተጨማሪ መረጃ፡

https://www.fanabc.com/ የግብርና-ዘርፍ-የወጪ-ንግድ-አፈፃፀም-የእ/

◆

ያለማስያዣ ብድር...(ከገፅ 2 የዞረ)

በመቶ ያነሰ መሆኑንም አመልክተዋል። ይህም በመንግሥት ዘርፍ የብድር አቅርቦት መጨናነቅና በጥቃቅንና አነስተኛ ቢዝነሶች ዘንድ ከፍተኛ የብድር ፍላጎት ካለመኖሩ ጋር የተያያዘ ነው።

የፋይናንስ ተቋማት ብድር ለመስጠት የተለያዩ መሥፈርቶችን የሚያስቀምጡት ታማኝ የብድር አሰጣጥ ሒደት ባለመኖሩ እንደሆነም ያመለከቱት አቶ ደርቤ፣ ይህን መቀየር እንደሚያስፈልግ አመልክተዋል።

እንዲህ ዓይነቱን ታሪክ ለመቀየር በኢትዮጵያ የመጀመርያ ነው የተባለውን ካለማስያዣ ብድር ለማቅረብ የሚያስችል አሠራር ለመዘርጋት የኦሮሚያ የኅብረት ሥራ ባንክ አኃዱ ብሏል።

ባንኩ ካለ ማስያዣ ብድር ለማቅረብ የሚያስችለውን አሠራር ለመተግበር የተነሳው ደግሞ ቴክኖሎጂን ድጋፍ በማድረግ ነው።

ይህንን አገልግሎት ወደ ተግባር ለመቀየር የኦሮሚያ ኅብረት ሥራ ባንክና ክፍያ ፋይናንስ ቴክኖሎጂስ በኢትዮጵያ የመጀመርያ የሆነውን ‹‹ምቹ ዲጂታል ያለ ዋስትና የብድር አገልግሎት›› ሥራ ላይ አውሏል።

የአገልግሎቱን መጀመርም የኩባንያዎቹ የሥራ ኃላፊዎች በሰጡት መግለጫ አስታውቀዋል።

የኦሮሚያ ኅብረት ሥራ ባንክና ክፍያ ፋይናንሺያል ቴክኖሎጂ አዲስ አጋርነት ‹‹ምቹ›› የሚል ስያሜ የተሰጠው ዲጂታል የብድር አገልግሎት አርተፊሻል ኢንትለጀንስ የሚንቀሳቀስ ዲጂታል የብድር ፕላት ፎርም ሲሆን፣ በኢትዮጵያ የመጀመርያውን ያለ ዋስትና የብድር ዓይነት የሚያመቻች ይሆናል ተብሏል።

በሁለቱ ኩባንያዎች መካከል በተደረገ ስምምነት መሠረት ባንኩ የክፍያን ዲጂታል የብድር ቴክኖሎጂ እንዲጠቀምና ክፍያ ደግሞ የኦሮሚያ ኅብረት ሥራ ባንክን ተደራሽነትና የፋይናንስ አቅምን እንዲጠቀም የሚያስችል ነው። ባንኩ በጥቃቅን፣ አነስተኛና መካከለኛ ቢዝነሶች ላይ ያነጣጠረ የብድር አገልግሎቶችን በማቅረብ፣ መሠረታዊና አመቺ የብድር አሰጣጥ ሥርዓቶችን በመከተል የሚሠራ ሲሆን፣ አገልግሎቱም በሞባይል ስልክ ብቻ ብድር መጠየቅና መፈቀድ የሚያስችል ይሆናል።

የኦሮሚያ የኅብረት ሥራ ባንክ ፕሬዚዳንት አቶ ደርቤ፣ እንዲህ ያለው አገልግሎት ለየት የሚያደርገው ሞባይልን በመጠቀም ብቻ ያለ ማስያዣ ብድር ማቅረቡ ብቻ ሳይሆን አገልግሎቱ ከሰዎች ንኪኪ ውጪ በሆነ መንገድ የሚሰጥ በመሆኑ ነው።

የብድሩ ማመልከቻ ሒደት ከብቁነት መሥፈርቶች ጀምሮ እስከ የብድር አከፋፈል ሒደት በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ ማጠናቀቅ የሚያስችል ሲሆን፣ ይህም ሥራ ከሰው ንኪኪ ውጪ በሆነ መንገድ የሚሠራ ይሆናል።

‹‹በኢኮኖሚው ዘርፍ ከፍተኛ ሥፍራ እያላቸው፣ ብዙ ትኩረት ያልተሰጣቸው፣ ጥቃቅን፣ አነስተኛና መካከለኛ ንግዶች ከክፍያ ጋር በአጋርነት በመሥራት የዲጅታል የፋይናንስ አቅርቦታችንን በማስፋት የፋይናንስ አገልግሎት ለማድረስ በመቻላችን ደስተኞች ነን፤›› ብለው፣ አገልግሎቱ በኢንዱስትሪ ውስጥ አዲስ ነገር የሚፈጥር እንደሆነም ጠቅሰዋል።

በተለይም ጥቃቅን፣ አነስተኛና መካከለኛ ቢዝነስ ውስጥ ለሚገቡ ኢንተርፕራይዞች እንዲሁም በየመንገዱ አነስተኛ የገንዘብ እንቅስቃሴ የሚያደረጉበት ቢዝነስ ዘርፎች ያላቸውን አቅም አሟጠው እንዲጠቀሙ ፋይናንስ ያስፈልጋቸዋል።

እነዚህ ቢዝነሶች መጫወት ያለባቸውን ሚና ላለመጫወታቸው አንዱ ምክንያት የብድር አገልግቶት ለማግኘት ያለመቻላቸው መሆኑን የጠቀሱት ፕሬዚዳንቱ፣ ለእነዚህ ዘርፎች ብድር ከማቅረብ አኳያ ኢትዮጵያ ውስጥ ትልቅ ችግር መኖሩንም ጠቁመዋል።

በኢትዮጵያ እነዚህ ዘርፎች በእጅጉ በፋይናንስ ችግር በሥራ ማስኬጃ እጥረት እየተፈተኑ ነው። እየተፈተኑ ብቻ ሳይሆን ከሳሃራ በታች የአፍሪካ አገሮች አንፃር ሲታይ በኢትዮጵያ በእነዚህ ዘርፎች ላይ ያለው ችግር በእጅጉ የጎላ መሆኑንም ጥናቶች ያሳያሉ።

ስለዚህ የኦሮሚያ ኅብረት ሥራ ባንክ እንደ ባንክ ደሃን የመደገፍ ዓላማ ያለው በመሆኑ፣ ባንኩ ምቹ የሚባለውን በዲጂታል የታገዘ ያለ ማስያዣ ብድር የመስጠት አገልግሎት ይዞ ሊቀርብ መቻሉ ተጠቅሷል። ይህ የብድር ዓይነት ዋስትና ማቅረብ የማይችሉ ጥቃቅን ሥራዎችን የሚሠሩ ግለሰቦች፣ አርሶ አደሮች በአነስተኛ ቢዝነስ ላይ የተሰማሩ በመካከለኛ ንግድ ላይ ለተሰማሩ ማኅብረሰብ ክፍሎች በቀላሉ በቴክኖሎጂ የታገዘ የብድር አገልግሎት የሚያገኙበት ነው።

ይህ አሠራር ብድር ከጠየቁበት ወቅት ጀምሮ ተፈቅዶ እስኪመለስ ድረስ ያለምንም የሰው ጣልቃ ገብነት ወይም ወደ ቅርንጫፍ ሳይሄዱ አገልግሎት የሚገኝበት መሆኑን አቶ ደርቤ ገልጸዋል።

‹‹ከኦሮሚያ ኅብረት ሥራ ባንክ ጋር ያደረግነው አጋርነት ለኢትዮጵያ ዲጅታል ኢኮኖሚ የምሥራች ነው፤›› ያሉት የክፍያ ቴክኖሎጂ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ሙኒር ዱሪ በበኩላቸው፣ ቴክኖሎጂው በአገሪቱ ውስጥ ያለ ማስያዣ ብድር የሚሰጥ መሆኑንም አመልክተዋል።

በኤአይ በታገዘ የብድር ደረጃ ምዘና ፕላት ፎርም በመጠቀም በኢትዮጵያ ለጥቃቅን፣ ለአነስተኛና ለመካከለኛ ንግድ ዘርፍ ያለ ማስያዣ ብድር እንደሚሰጥ ተስፋ እንዳላቸውም ገልጸዋል።

ማይክሮ ብድር የመንገድ ዳር ነጋዴዎችና ሌሎች ጥቃቅን ቢዝነሶች ላይ ትኩረት ያደረገ ሲሆን፣ አሁን በአጋርነት ያለ ማስያዣ የሚቀርበው ብድር፣ ከፍተኛ የብድር መጠን 30,000 ብርና ከአንድ እስከ አራት ወራት የጊዜ ገደብ ውስጥ የሚመለስ እንደሆነም ተገልጿል።

ለአነስተኛና መካከለኛ ደረጃ ነጋዴዎች ደግሞ ከፍተኛ የብድር መጠን 150,000 ብር ሲሆን፣ የመክፈያ ጊዜ እስከ አንድ ዓመት ድረስ ነው። ከዚህም በላይ ብድሮቹ ለጥቃቅን እንዲሁም ለአነስተኛና ለመካከለኛ ቢዝነሶች የሥራ ካፒታል ለመሸፈን የታቀደ ስለመሆኑ የሚያመለክተው የኩባንያዎቹ የጋራ መግለጫ፣ በተጨማሪም በተለያዩ የድርጅት ሠራተኞች ላይ ያተኮረ ለተለያዩ ጉዳዮች የሚውል የብድር አገልግሎት የሚሰጥበት ይሆናል።

ይህ ያለ ዋስትና የሚሰጥ ዲጂታል የብድር አገልግሎት፣ አዲስ የብድር አገልግሎት ፈጠራ፣ ፈጣን ሒደት ያለው፣ መስያዣ የማይጠየቅበትና በማንኛውም ጊዜና በማንኛውም ቦታ ተደራሽ የሆነ አገልግሎትና ፕላት ፎርሙ የብድር ብቁነትንና ተለዋዋጭ የመክፈያ ዘዴን ለመወሰን ዳታ የሚጠቀም ነው ተብሏል።

የምቹ ዲጂታል የብድር አገልግሎት በሙከራ ጊዜ የኦሮሚያ ኅብረት ሥራ ባንክ ተበዳሪዎችን በ30 በመቶ ከፍ ያደርጋል ተብሎ የሚጠበቅ ስለመሆኑም ተገልጿል።

የፋይናንስ አገልግሎቶች በዋነኝነት ያተኮሩትና በትልልቅ ኢንተርፕራይዞች ላይ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የገጠሩ ሕዝብ በተለይም አርሶ አደሮች፣ አነስተኛ የንግድ ተቋማት ባለቤቶችና ማኅበረሰቦች ከባንክ አገልግሎት የተገለሉ እንደነበሩ ያስታወሱት አቶ ደርቤ፣ ያለ ወለድ ብድር መስጠት ባንኩን ችግር ውስጥ አይከተውም ወይ ተብሎ ለቀረበላቸው ጥያቄ እንዲህ እየተሠጋ ሥራ የማይሠራ መሆኑን ገልጸዋል።

ያለ ማስያዣ የሚሰጠውን ብድር ወስደው ተበዳሪዎች ቢጠፉ የባንኩ ዕጣ ፈንታ ምን ሊሆን ነው? ለሚለው ጥያቄም፣ ‹‹ላለፉት በርካታ ዓመታት በባንክ ኢንዱስትሪ ውስጥ የመጀመርያው ፍርኃት ከዋስትና ጋር የተገናኘ ነው፣ ዋስትና ከሌለ ብድር አይሰጥም። በማስያዣነት ከሚጠይቁ መካከል አንዱ ቤት ነው። ቤት ለመሥራት

የጥጥ ዋጋ ከሦስት እጥፍ በላይ በመጨመሩ መቸገራቸውን የጨርቃ ጨርቅ አምራቾች ገለጹ

በጥጥ ምርት አቅርቦት እጥረትና እስከ ሦስት እጥፍ በሚደርስ የዋጋ ጭማሪ ምክንያት ችግር እንደገጠማቸው፣ የጨርቃ ጨርቅ አምራቾች ተናገሩ።

በአዳማ ዴቨሎፐመንትስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ኩባንያ የጥራት ቁጥጥር ክፍል ኃላፊ አቶ ታጠቅ ግርማ ለሪፖርተር እንደገለጹት፣ በጥጥ ላይ ካለፈው ዓመት ጀምሮ የዋጋ ጭማሪ እየታየ እንደነበር ገልጸው፣ በተለይ በ2014 ዓ.ም. ከፍተኛ የሚባል የዋጋ ጭማሪ መኖሩን አስረድተዋል።

እንደ አቶ ታጠቅ ገለጻ፣ የጥጥ ዋጋ በኩንታል ከአምስት ሺሕ ብር አይበልጥም ነበር። በአሁኑ ወቅት ግን አንድ ኩንታል ጥጥ 17,000 ብር እየተሸጠ መሆኑን፣ ለዚህም በተለይ ምርቱ በበቂ መጠን በገበያ ውስጥ አለመገኘቱ ምክንያት መሆኑን ገልጸዋል።

የጥጥ አቅርቦት በዋነኛነት በአዋሽ ተፋሰስ አካባቢዎችና በመተማ የሚገኝ መሆኑን፣ በተለይ በ2013 ዓ.ም. የአዋሽ ወንዝ ባደረሰው የጎርፍ አደጋ ምክንያት በጥጥ ምርት ላይ ጉዳት በመድረሱ የአቅርቦት እጥረት መፈጠሩን አቶ ታጠቅ ገልጸዋል።

በፋብሪካቸው በዓመት እስከ 30 ሺሕ ኩንታል ጥጥ የመጠቀም አቅም ቢኖራቸውም፣ በአቅርቦት እጥረት ምክንያት በቂ ምርት ለማግኘት ባለመቻላቸው ከተለያዩ የምዕራብ አፍሪካ አገሮች ለማስገባት በጥናት ላይ መሆናቸውን ገልጸዋል።

‹‹ከዚህ በፊት ብዙም ባልተለመደ ሁኔታ በጥጥ ግብይት ላይ የደላሎች ተፅዕኖ እየታየ ነው፤›› ያሉት አቶ ታጠቅ፣ ይህም ለዋጋው አለመረጋጋት ተጨማሪም መንስዔ ሆኗል ብለዋል።

ቀደም ሲል የአንድ ኪሎ ግራም ጥጥ ዋጋ እስከ 50 ብር እንደነበር የገለጹት የዕድገት ድርና ማግ ፋብሪካ የክትትል ክፍል ኃላፊ አቶ ሰለሞን አበበ፣ በአሁኑ ወቅት የአንድ ኪሎ ግራም የጥጥ ዋጋ እስከ 170 ብር እየተሸጠ መሆኑን ተናግረዋል።

የአዋሽ ወንዝ በ2013 ዓ.ም. ክረምት ባደረሰው ጉዳት ምክንያት ምርቱ እንደጠፋና ዋጋ እንደጨመረ ጠቅሰው፣ አሁንም ድረስ ተፅዕኖ እያሳደረ ነው ብለዋል። ነገር ግን የደረሰውን የጎርፍ አደጋ ሰበብ በማድረግ ደላሎች በመሀል እየገቡ ዋጋ እንዲጨምር እያደረጉ እንደሆነም ጠቁመዋል።

ሪፖርተር ያነጋገራቸው የኢትዮጵያ ጥጥ አምራቾች ማኅበር ፕሬዚዳንት አቶ መልካሙ ተላከ በበኩላቸው፣ የጥጥ አቅርቦት እጥረትና የዋጋ ጭማሪ መኖሩን ገልጸዋል። እጥረቱ የተከሰተው በተለይ በ2014 ዓ.ም. የምርት ዘመን የሚሰበሰበው ጥጥ ተጠናቆ ወደ ገበያ ባለመግባቱ እንደሆነ አክለዋል።

የ2013 ዓ.ም. ምርትም በተለይ በአዋሽ ወንዝ የጎርፍ አደጋ በመጥፋቱ፣ እንዲሁም በቤኒሻንጉል ጉሙዝና በሁመራ ያሉ አምራቾችም በወቅታዊ ችግር ምክንያት ማምረት በማቆማቸው ለጥጥ አቅርቦት እጥረትና ለዋጋ ጭማሪ ምክንያት መሆኑን ተናግረዋል።

‹‹ገበያውን በተመለከተ ደላሎች ገብተውበታል በሚለው ሐሳብ ላይ እስካሁን የተመለከትኩትም ሆነ የደረሰኝ መረጃ የለም። ነገር ግን አርሶ አደሮችም ሆኑ አምራቾች ቀጥታ ለፋብሪካዎች የሚያደርሱበት አማራጭ ስላለ የደላሎቹ ተፅዕኖ ከፍተኛ ነው ብዬ አላስብም፤›› ብለዋል።

ፋብሪካዎች በዓመት እስከ 50 ሺሕ ሜትሪክ ቶን የተዳመጠ ጥጥ እንደሚጠቀሙ የገለጹት በኢትዮጵያ ጨርቃ ጨርቅ ልማት ኢንስቲትዩት የጥጥ ልማት ዘርፍ ኃላፊ አቶ መሰለ መኩሪያ፣ በ2013 ዓ.ም. የተመረተው ጥጥ 35 ሺሕ ቶን ብቻ መሆኑን አስታውቀዋል።

ለምርቱ ማነስ በዋነኛነት ሁመራ አካባቢ የሚገኙ የጥጥ እርሻዎች በፀጥታ ምክንያት ባለማምረታቸው፣ እንዲሁም በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል የተመረተ ጥጥ በፀጥታ ችግር ምክንያት በመቃጠሉ እንደሆነ አብራርተዋል።

የተፈጠረውን የአቅርቦት እጥረት የዋጋ ጭማሪ ለማረጋጋት አሥር ሺሕ ሜትሪክ ቶን ጥጥ ከውጭ ለማስመጣት፣ በኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ ◈ ግብዓቶች ልማት ድርጅት በኩል ጨረታ መውጣቱን ገልጸዋል።

ከዚህ በተጨማሪም አሁን በመሰብሰብ ላይ ያለው የጥጥ ምርት እስከ ጥር 30 ቀን 2014 ዓ.ም. ድረስ ተጠናቆ፣ ለፋብሪካዎች ለማቅረብ ዝግጁ ይደረጋል ብለዋል።

በኢትዮጵያ የሚገኙ የጨርቃ ጨርቅ አምራቾች በዓመት ከ100 ሺሕ ቶን በላይ ጥጥ የመጠቀም አቅም ቢኖራቸውም፣ አሁን እየቀረበ የሚገኘው ከግማሽ በታች እንደሆነ አቶ መሰለ አስረድተዋል።

በግንባታ ዘርፍ የሚያጋጥሙ አለመግባባቶችን የሚፈታ ቦርድ ሊቋቋም ነው

በግንባታ ዘርፍ ውስጥ የሚያጋጥሙ አለመግባባቶችን የሚፈታ ቦርድ ሊቋቋም መሆኑን፣ የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ባለሥልጣን አስታወቀ።

ይህ የተገለጸው ጥር 24 ቀን 2014 ዓ.ም. በስካይላይት ሆቴል የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ባለሥልጣን፣ በግንባታ ዘርፍ ያሉ ችግሮችን በተመለከተ ያስጠናው ጥናት ሲቀርብ ነው።

ባለሥልጣኑ በግንባታው ዘርፍ በተቋራጮችና በግንባታ አሠሪዎች መካከል እየተፈጠሩ ያሉትን አለመግባባቶች ለመፍታት ያስችላል ያለውን ቦርድ ለማቋቋም የወሰነው፣ ባለፉት ዘጠኝ ወራት ባስጠናው ጥናት መነሻነት መሆኑ ተገልጿል።

ጥናቱ በተለይ በሕንፃ ተቋራጮችና በባለቤቶች መካከል በግንባታ መጓተት፣ በጥራት፣ በዲዛይን ለውጥና በሌሎችም ምክንያቶች በሚፈጠሩ አለመግባባቶች ግንባታዎች ለዓመታት እንደሚቋረጡ፣ የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር መስፍን ነገዎ (ኢንጂነር) ገልጸዋል።

ጥናቱ የተደረገው ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ከአዳማ ዩኒቨርሲቲ፣ ከጅማ ዩኒቨርሲቲና ከሐዋሳ ዩኒቨርሲቲ በተውጣጡ ምሁራን አማካይነት መሆኑን፣ በጥናቱ መሠረትም በግንባታ ዘርፍ ውስጥ የሚፈጠሩትን አለመግባባቶች ለመፍታት በፍርድ ቤት የሚደረጉ የክስ ሒደቶች የተጓተቱና ለተጨማሪ ወጪ የሚዳርጉ በመሆናቸው፣ ፍርድ ቤት ከመድረሳቸው በፊት በቦርድ መፍታት የተሻለ አማራጭ መሆኑ በጥናቱ ግኝት ተመላክቷል ብለዋል።

የጥናት ቡድኑ መሪ ውብሸት ዝቅአለ (ዶ/ር) ጥናቱ በመንገድ፣ በሕንፃ፣ በውኃና በሌሎችም ዘርፎች የሚገኙ 248 ፕሮጀክቶች ላይ የተደረገ መሆኑን ገልጸው፣ ለ20 ዓመታት ያህል የተጓተቱ ፕሮጀክቶች መኖራቸውን ተናግረዋል።

በግንባታ ተቋራጮችና በአሠሪዎች መከካል የሚፈጠረው አለመግባባት፣ በአብዛኛው የቅድመ ሥራ ኮንትራትና የዲዛይን ዝግጅት በበቂ ሁኔታ ተጠናቆ ወደ ሥራ ባለመገባቱ እንደሆነ አውስተዋል። ይህም በተለይ የግንባታው ባለቤቶች በዋጋ ንረትና በዲዛይን ለውጦች ምክንያት ጥያቄ በማንሳት አለመግባባት ውስጥ እንዲገቡ ምክንያት ሆኗል ብለዋል።

አለመግባባቶቹን ለመፍታት የሚቋቋመው ቦርድ ወደ ፍርድ ቤት ከሚሄዱት ውስጥ፣ ቢያንስ 75 በመቶ የሚሆኑትን ውዝግቦች መፍታት እንዲችል መታሰቡን ውብሸት (ዶ/ር) ጠቁመዋል።

በጥናቱ በርካታ አገሮች በግንባታ ሒደት የሚያጋጥሙ አለመግባባቶችን የሚፈቱበት መንገድ እንደ ልምድ የተወሰደ ሲሆን፣ ከእነዚህም መካከል ኬኒያ፣ ናይጄሪያና አንጎላ ይገኙበታል።

ቦርዱን ለማቋቋም ከፍትሕ ሚኒስቴር፣ ከጠቅላይ ፍርድ ቤትና ከሌሎች ባለድርሻዎች ጋር በመሆን ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ለማቅረብ በዝግጅት ላይ እንደሚገኙ አቶ መስፍን ተናግረዋል።

የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስትሯ ወ/ሮ ጫልቱ ሳኒ በበኩላቸው፣ እየተስፋፋ ከመጣው ከተሜነትና የግንባታ ዘርፍ አንፃር አሁን ያሉ ችግሮች በአፋጣኝ የሚፈቱበት አማራጭ መፈለግ ተገቢ ነው ብለዋል።

ከአገሪቱ በጀት እስከ 60 በመቶ ያህሉን የግንባታው ዘርፍ እንደሚይዝ የገለጹት ሚኒስትሯ፣ በዚህ ዘርፍ ◈ የሚያጋጥመው መጓተትና ከፍተኛ ብክነት

ዳያስፖራዎች በኢንቨስትመንት ጉዳይ ላነሱት የደኅንነት ሥጋት መንግሥት ምላሽ ሰጠ

የመንግሥትን ጥሪ ተከትለው ወደ አገር ቤት የተመለሱ ዳያስፖራዎች ኢንቨስትመንትን አስመልክቶ በተለያዩ መድረኮች ላይ ያነሷቸውን የደኅንነት ሥጋቶች በተመለከተ መንግሥት ምላሽ ሰጠ።

በአገሪቱ ኢንቨስት እንዲያደርጉ የተለያዩ አማራጮች ሲቀርብላቸው የቆዩት ዳያስፖራዎች እንቅፋት ይሆናሉ ብለው ካነሷቸው ጉዳዮች ውስጥ አንዱ፣ በአገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች የሚፈጠሩ ግጭቶችን ተከትሎ የሚመጣውን የደኅንነት ሥጋት ነው። ዳያስፖራዎቹ የድምፃዊ ሃጫሉ ሁንዴሳን ሞት ተከትሎ በሻሸመኔ ከተማ የደረሰውን ውድመት በማሳያነት ያነሱ ሲሆን፣ መንግሥት ዳያስፖራዎች ኢንቨስት እንዲያደርጉ ጥሪ ሲያደርግ ለሚፈጠሩ የደኅንነት ሥጋቶች ምን ዓይነት ጥበቃ ሊያደርግ እንዳሰበ ጠይቀዋል።

ጥር 6 ቀን 2014 ዓ.ም. በተዘጋጀው የማኑፋክቸሪንግ ዘርፍና የዳያስፖራ ትስስር መድረክ ላይ ተገኝተው ለዚህ ሥጋት ምላሽ የሰጡት የኢንዱስትሪ ሚኒስትሩ አቶ መላኩ አለበል፣ የፀጥታ ችግር ቢኖርም ‹‹እንዳናጋንነው›› ብለዋል። ኢትዮጵያ ውስጥ ስላለው የፀጥታ ችግር ሲነሳ ኬንያ፣ ደቡብ አፍሪካና ናይጄሪያ ያሉ አገሮች ግምት ውስጥ መግባት እንዳለባቸው ተናግረዋል። ‹‹የወርቅ ጌጥ አድርጋችሁ እንደፈለጋችሁ የምትንቀሳቀሱበት ከተማ አዲስ አበባ እንጂ ናይሮቢ ወይም ዳሬሰላም አይደለም፤›› ብለዋል።

ከዚህም ባሻገር መንግሥት የደኅንነት ሥጋቶችን ለመቅረፍ ከሚያከናውነው ሥራ ባሻገር የሃይማኖት ተቋማት ያላቸው ሚናም መታሰብ እንዳለበት አስረድተው፣ ማኅበረሰቡ ዝርፊያንና ስርቆትን በተመለከተ ያለው አቋም ሥጋቶችን ለመቅረፍ ድርሻ እንዳለው ገልጸዋል። ‹‹አሁን ያሉ የፀጥታ ችግሮች ዕለታዊና መንግሥትና ሕዝብ ተባብረው ሊፈቱ የሚችሏቸው ስለሆኑ፣ ዳያስፖራው በዚህ መረበሽ የለበትም፤›› ብለዋል።

በዳያስፖራዎች የተነሳው ሌላው ችግር የመንግሥት መዋቅር ውስጥ ያለው የሙስና ችግር ሲሆን አቶ መላኩ በትክክል ችግሩ እንዳለ አውስተው፣ ሙስና የመንግሥት ተቋም ውስጥ ብቻ ሳይሆን ሃይማኖት ተቋም ውስጥም ገብቷል ብለዋል። ይኼንን ችግር ለመቅረፍ ከሰው ንክኪ የራቀ ዲጂታል ሥርዓት መዘርጋትን እንደ መፍትሔ ያቀረቡት ሚኒስትሩ፣ ዳያስፖራው ይኼንን ሥርዓት ለመዘርጋት ማገዝ እንዳለበት አሳስበዋል።

በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ያሉትን አማራጮች ለዳያስፖራዎች ለማቅረብ በተዘጋጀው በዚህ ፕሮግራም ላይ በአግሮ ፕሮሰሲንግ፣ በቆዳና የቆዳ ውጤቶች፣ በጥጥ፣ በጨርቃ ጨርቅና በአልባሳት ዘርፎች ያሉት አማራጮች ቀርበዋል። ኢትዮጵያ ውስጥ በእነዚህ ዘርፎች ለመሰማራት የሚያስችል ሀብት ቢኖርም ዘርፎቹ በሚፈለገው መጠን ማደግ

ባንኮች የደንበኞቻቸውን ዝርዝር መረጃ የመያዣ ጊዜና የታዩ ክፍተቶች

አቶ ገነነ ሩጋ

አቶ አቢ ሳኖ

አቶ ደርቤ አስፋው

አቶ ደረጀ ዘበበ

በኢትዮጵያ በሥራ ላይ ከሚገኙ 20 ባንኮች ውስጥ የቁጠባ ሒሳብ የከፈቱ ደንበኞች ቁጥር ከ66 ሚሊዮን በላይ ደርሷል። ይህ ቁጥር በአንድ ባንክ ሁለትም ሦስትም አካውንት ያላቸውንም የሚያጠቃልል ነው። ይህንን ያህል ቁጥር የደረሱ የባንክ ደንበኞችን የተሟላ መረጃ መያዝ አስፈላጊነት ታኖበት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ከስድስት ወራት በፊት አንድ መመርያ አውጥቷል።

መመርያው ባንኮች የደንበኞቻቸውን ዝርዝር መረጃ በሚገባ በማጣራትና በማደራጀት በመረጃ ቋት ውስጥ መያዝ እንደሚገባቸው የሚያስገድድ ነው። ይህ ድንጋጌ መተግበር የሚገባው በስድስት ወራት ውስጥ ሲሆን፣ በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ የባንክ ደንበኞች ሁሉ በመመርያው መሠረት የሚጠበቅባቸውን መረጃ ደንበኛ ለሆኑበት ባንክ በአካል ቀርበው መስጠትና የተዘጋጀውን ፎርም መሙላት ይኖርባቸዋል።

በመመርያው ድንጋጌ መሠረት የደንበኞችን መረጃ የመቀበልና የማደራጀት ሥራ የተቀመጠለት የጊዜ ገደብ የሚጠናቀቀው የካቲት 20 ቀን 2014 ዓ.ም. ነው።

ባንኮች በዚሁ መመርያ መሠረት ይህንን አገልግሎት የሚሰጥ ክፍል አደራጅተው የደንበኞቻቸውን መረጃዎች እያሰባሰቡ ነው። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ያወጣውን ይህንን መመርያ ተከትለው ደንበኞቻቸው ወደ ባንክ ቀርበው የተጠየቀውን መረጃ እንዲሰጡም በተለያዩ መንገዶች መልዕክት እያስተላለፉ ይገኛሉ።

የንብ ኢንተርናሽናል ባንክ ፕሬዚዳንት አቶ ገነነ ሩጋ፣ ይህንን መመርያ ለመተግበር በተለያዩ የመገናኛ ብዙኃንና በሌሎች የመረጃ መቀበያ ዘዴዎች ደንበኞቻቸው የባንክ ደብተር ወደ ከፈቱበት ቅርንጫፍ ቀርበው በመመርያው የተጠቀሰውን መረጃዎች እንዲሞሉ እየተደረገ ነው ይላሉ። እስካሁን ባለው ሒደት በብዛት የባንክ አገልግሎት ለማግኘት ሲመጡ ይህንኑ መረጃ እንዲሞሉ የሚደረግ መሆኑንም አክለዋል።

የዘመን ባንክ ፕሬዚዳንት አቶ ደረጀ ዘበነም የአቶ ገነነን ሐሳብ ተጋርተው ደንበኞቻቸውን መመርያውን ተከትለው እያስተናገዱ ነው። እስካሁን የመረጃ አሰባሰቡ በጥሩ ሁኔታ እየሄደላቸው ስለመሆኑም ይገልጻሉ።

እንደ አቶ ደረጀ ገለጻ፣ ደንበኞች በግንባር ቀርበው መረጃውን እንዲሰጡ በሚዲያ ከማስነገር ባለፈ በስልክ ጭምር እየነገሩ መሆኑ ነው። በዚህ ሒደት አንዳንዶች በተደወለላቸው ስልክ የማይገኙ መሆኑን መገንዘብ ስለመቻላቸው እኚሁ የሥራ ኃላፊዎች ይገልጻሉ። ሆኖም እስካሁን ባለው ሒደት አብዛኛውን ደንበኞቻቸውን እያደረሱ መሆኑን በመግለጽ እስከተቀመጠው የጊዜ ገደብ ደረስ ይህንኑ እየሠሩ መሆኑን ያመለክታሉ።

የኦሮሚያ ባንክ ፕሬዚዳንት አቶ ተፈሪ መኮንንና አቶ ገነነም ብዙ ደንበኞች በመስተናገዳቸው በቀረው ጊዜ ቀሪዎቹን ደንበኞቻቸውን ለመድረስ ይቻላል የሚለውን እምነታቸውን አንፀባርቀዋል።

ይሁን እንጂ ብዙዎቹ ባንኮች በአዲሱ መመርያ መሠረት ደንበኞቻቸውን ተቀብለው እያስተናገዱ ቢሆንም፣ አንዳንድ ደንበኞች በተለይ ወርኃዊና ዓመታዊ ገቢውን ከማሳወቅ ጋር ተያይዞ ተደጋጋሚ ጥያቄዎች የሚቀርቡላቸው መሆኑን አመልክተዋል። ዓመታዊ ገቢያቸውን ለመገመት ያልቻሉም ይህንን መመርያ ለመፈጸም ፈራ ተባ ማለታቸውን የሚገልጹም አሉ።

ሌሎች የሚጠየቁ መረጃዎች በአግባቡ ተሞልተው ውርኃዊና ዓመታዊ ገቢ ምን ያህል እንደሆነ በሚያመለክተው የመረጃ ሥፍራ ብዙዎች የሚቸገሩ ስለመሆኑም ለመገንዘብ ተችሏል። ሆኖም ባንኮች ዕገዛ በማድረግና ማብራሪያ በመስጠት የገቢያቸውን መጠን እንዲሞሉ እየተደረገ እንደሚገኝ ካነጋገርናቸው የባንክ ኃላፊዎች ማብራሪያ ለመረዳት ተችሏል።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ይህንን መመርያ ያወጣው የፋይናንስ ተቋማት ደንበኞቻቸውን ስለሚያውቁበት ሁኔታ በአገራቸው ብሔራዊ መታወቂያ ባለመኖሩ ከባንክ ሒሳብ መክፈት፣ ከገንዘብ መክፈልና ማስቀመጥ ጋር የተያያዙ በርካታ ችግሮች የሚታዩ መሆኑን በመግለጽ እንደሆነ ይታወቃል። በጥቁር ገበያና በሌሎች ሕገወጥ ተግባራት የተሰማሩ አካላትም ይህንኑ ክፍተት ሲጠቀሙበት የቆዩ በመሆኑ እንዲህ ያሉ ችግሮችን ለመቅረፍ ታልሞ የወጣ ነው።

ችግሮችን በዘላቂነት ለመከላከል አዲስ የተጀመረው ብሔራዊ መታወቂያ ለዜጎች የመስጠት ሒደቱ እስኪደርስ የፋይናንስ ተቋማት ለደንኞቻቸው የተለየ የደንበኛ መለያ ቁጥር እንዲሰጡ ባንኮችን የሚያስገድድ መሆኑንም መመርያው ያመለክታል። በዚህ መለያ ቁጥር አማካይነት የአንድ ባንክ ደንበኛ በባንኩ የተለያዩ ቅርንጫፎች ብዙ ሒሳብ ቢኖረውም፣ እንደ አንድ ደንበኛ እንዲታወቅ ለማድረግ እንዲቻል ታስቦም የወጣው ይህ መመርያ ተፈጻሚ እንዲሆን የተሰጠው የስድስት ወራት ጊዜ የቀረው ከአንድ ወር ያነሰ ጊዜ ነው። ቀነ ገደቡ ወደ ማለቁ ቢሆንም፣ አሁንም ተገቢውን መረጃ ለባንክ ያልሰጡ ደንበኞች ቁጥራቸው ቀላል እንደማይሆን ስለሚታመን ባንኮች ተከታታይ ማስታወቂያዎችን እያወጡ ነው።

በመመርያው መሠረት ባንክ ቀርበው ተገቢውን መረጃ ያለማሟላታቸውንና በአራት ባንኮች የቁጠባ ሒሳብ እንዳላቸው የገለጹት ተገልጋይ እስካሁን መረጃን አሟልተው ያልሰጡት ፎርሙ ላይ ወርሃዊና ዓመታዊ ገቢን መግለጽ ግዴታ ሆኖ በመቀመጡ ነው ይላሉ።

እንደ እሳቸው ገለጻ፣ ችግራቸው ገቢን ማሳወቁ እንደ ግዴታ የተቀመጠ መሆኑ ሳይሆን፣ ከደመወዜ ሌላ ዓመታዊ ገቢዬን ይህን ያህል ነው በሚል በትክክል ማስቀመጥ ባለመቻላቸው ነው።

‹‹በአራቱም ባንኮች ውስጥ ባለ አክሲዮን ነኝ፤›› ያሉት እኚህ የተለያዩ ባንኮች ደንበኛ ባለአክሲዮን፣ ከእነዚህ ባንኮች የሚያገኙት ዓመታዊ የትርፍ ድርሻ በአካውንታቸው ሲገባ የቆየ ሲሆን፣ ነገር ግን እነዚህ ባንኮች በየዓመቱ የሚከፍሉት የትርፍ ክፍፍል መጠን ምን ያህል እንደሆነ ባላወቁበት ሁኔታ ዓመታዊ ገቢያቸውን ይህንን ያህል ነው ብዬ ለመግለጽ ስለተቸገሩ ፎርሙን መሙላት እንዳልቻሉ ይገልጻሉ።

‹‹ባንኮች ዓመታዊ የትርፍ ድርሻቸው ስለሚለያይ የሚገኘውን ዓመታዊ ትርፍ መጠን ምን ያህል እንደሆነ ሳላውቅ ገቢዬ ይኼን ያህል ነው ብሎ ለመሙላት በመቸገሬ በአንድ ባንክ ከአካውንቴ ላይ ብቻ የደመወዝ መጠኔን ገልጫለሁ። የሌሎቹን እስካሁን አልሞላሁም፤›› ይላሉ።

እንዳነጋገርናቸው የሥራ ኃላፊዎች ከሆነ፣ እንዲህ ያለ ሁኔታ ሲያጋጥም ደንበኛው አማካይ ገቢውን አስቀምጦ ትክክለኛ ገቢው ቢታወቅ ማስተካከል የሚቻልበት ዕድል አለ። ይህ ጉዳይ ችግር አለው ብለው እንደሚያምኑ የሚገልጹት አቶ ደረጀ ደግሞ፣ የተለያዩ የገቢ ምንጫቸውን በማሥላት ገቢያቸውን ማስመዝገብ ይኖርባቸዋል ይላሉ። ባንኩ ዓመታዊ ገቢያቸውን ሊያጣራ የሚችልበት ሁኔታ የተገደበ ቢሆንም፣ ደንበኞቻቸውን የሚያስተናግዱት በሰጡት መረጃ መሠረት እንደሆነም ገልጸዋል።

ገቢውን ማሳወቅ ያለበት ደንበኛው ነው። ለጊዜው የተለየ ሊመጣበት የሚችል ነገር የለም። አንድ ወቅት ላይ ግን ከገቢው በላይ የሆነ ገንዘብ ተንቀሳቅሷል ተብሎ ቼክ ሲደረግ፣ እሱ ከመደበኛ ገቢው በላይ ሌላ ተጨማሪ ገቢ እንዳለው ማሳያውን ማቅረብ አለበት እንጂ የሚከለክለው ነገር የለም።

መመርያው የሒሳቡ ባለቤት የሚታወቅ ሰው ነው ወይ? የሚለውን የሚመልስ መሆኑን የጠቆሙት አቶ ደረጄ፣ ለምሳሌ አንድ ሰው አካውንት ከፍቶ ሲፈልግ በፎርጅድ መታወቂያ ሌላ ሰው ሆኖ ይገኛል፣ ስለዚህ እንዲህ ያለውን ነገር ለማፅዳት ተብሎ የተዘጋጀ ነው ይላሉ።

ለተሰጠው መረጃ ኃላፊነቱን የሚወስደውም ደንበኛው መሆኑን ያመለከቱት አቶ ደረጄ፣ ዓመታዊ ገቢን አሥልቶ መረጃ መስጠት ግን ምንም ችግር የሌለውና ለሁሉም የሚጠቅም መሆኑንም አክለዋል። እንዲህ ዓይነቱ አሠራር በሌላው አገርም የሚተገበርና እየተሠራበት ያለ በመሆኑ፣ ደንበኞች ምንም ሥጋት ሊገባቸው እንደማገባም አመልክተዋል። በተለያዩ ባንኮች አካውንት ያላቸው ደንበኞችም የሚሰጡት መረጃ ተመሳሳይ መሆን እንደሚገባው አስረድተው፣ ይህ መመርያ ምንም ችግር የሌለው በመሆኑ የጊዜ ገደቡ ከማለቁ በፊት መረጃ መስጠት ጠቃሚ ነው ይላሉ።

ከዚህ ውጪ አንዴ የተሞላ መረጃ ዘለዓለም በቋሚነት የሚቀመጥ ሲሆን፣ ዓመታዊ ገቢው ሲቀንስና ሲጨምር ይህንኑ በማስታወቅ መረጃውን በየጊዜው ማስተካከል የሚቻልበት ዕድል ስለመኖሩ ከባንኩ የሥራ ኃላፊዎች ገለጻ ለመረዳት ተችሏል።

ሆኖም በዚሁ መመርያ ውስጥ እንደተቀመጠው የአጠራጣሪ ግለሰብ ወይም ድርጅት መረጃ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክና ለፋይናንስ መረጃ ደኅንነት ማዕከል መተላለፍ እንዳለበት በፋይናንስ ተቋማት ላይ ግዴታ የተጣለ በመሆኑ በዚሁ መሠረት እየተሠራ ነው ተብሏል። ይህ መመርያ ተፈጻሚ የሚሆንባቸው የፋይናንስ ተቋማት የደንበኞቻቸውን ሁኔታና ታሪክ የሚከታተል አዲስ አደረጃጀትና ዘመናዊ የቴክሎጂ አሠራር እንዲዘረጉ የሚያስገድድ በመሆኑም ባንኮቹ በዚሁ መሠረት አደራጅተው እየሠሩ መሆኑ ታውቋል።

ከባንክ የሥራ ኃላፊዎች መረዳት እንደሚቻለው፣ የባንክ ደንበኞች እስከተሰጠው የጊዜ ገደብ ድረስ በመመርያው መሠረት ማንነታቸውንና አጠቃላይ ገቢያቸውን፣ እንዲሁም ሌሎች በመመርያ በግዴታ የተቀመጡ መረጃ ካልሰጡ ከየካቲት 20 በኋላ ሒሳባቸውን ማንቀሳቀስ ይችላሉ? ወይስ አይችሉም? የሚለው ጥያቄ ላይ የተለያየ አመለካከት ይንፀባረቃል።

እንደ አቶ ደረጀ ገለጻ፣ ከቀነ ገደቡ በኋላ አካውንቱ መንቀሳቀስ አይችልም ይላሉ። ከዚያ በኋላ ደንበኛው ሄዶ ነው የሚያስተካክለው። በመመርያው መሠረት ደንበኛው መጥቶ ፎርሙን ካልሞላ አካውንቱን መጠቀም አይችልም። ሆኖም ከየካቲት 20 በኋላ በዚህ መመርያ ዙሪያ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የሚሰጠውም ተጨማሪ ነገር ካለ በዚያው የሚታይ እንደሚሆንም ጠቁመዋል።

በአንድ ግለሰብ ወይም በድርጅት ስም የባንክ ሒሳብ ሲከፍት፣ ገንዘብ ለማስቀመጥ ሲያስፈልግ፣ ከሒሳብ ወደ ሒሳብ ገንዘብ ማስተላለፍ ሲፈለግ፣ ገንዘብ ከባንክ ለማውጣትም ሆነ ለማስቀመጥ ለሚጠየቁ መረጃዎች ሁሉም የፋይናንስ ተቋማት ተመሳሳይ ቅፅ እንዲጠቀሙ ያስገድዳል። ይህም በፋይናንስ ተቋማቱ ያለውን ወጣ ገባ አሠራር ያስቀራል ተብሎ ታምኖ እየተሠራበት ነው።

የኦሮሚያ የኅብረት ሥራ ባንክ ፕሬዚዳንት አቶ ደርቤ አስፋው፣ ይህ መመርያ ◈ በትክክል መተግበሩ አገራዊ ጠቀሜታ ይኖረዋል ይላሉ። ባንካቸውም ባለው አቅም ይህንን የደንበኞቹን መረጃ በማጠናከር ሥራ ላይ መጠመዱንም ገልጸዋል። ሥራው ግን ቀላል ያለመሆኑን ያስረዱት አቶ ደርቤ፣ ገቢን ከማሳወቅ በላይ አንድን ደንበኛ ትክክለኛነት ለመለየት የሚሠራው ሥራ ከባድ ነው። ለምሳሌ ‹አበበ› የሚለውን ስም አንዳንዱ ፊደሎችን በመቀያየር ይጠቀማል። ይህንን የማጣራት ሥራ ቀላል አይደለም፣ ያደክማል። መጨረሻ ላይ ግን እንዲህ ያለው የጠራ አሠራር በንፅህና ለመሥራትና ደንበኞችን ለይቶ አስፈላጊውን አገልግሎት ለመስጠት ያስችላል ይላሉ።

የወጡ ሕጎችን ያላከበረ፣ የሚያጠራጥር መረጃ የሰጠ፣ አጠራጣሪ ክፍያ የፈጸመ ግለሰብ ወይም ድርጀት ከፋይናንስ ተቋማት ማንኛውንም አገልግሎት እንዲያገኝ ለፋይናንስ ተቋማት ሥልጣን የተሰጠ በመሆኑ ደንበኞች መረጃቸውን ካልሰጡ ባንኮች ዕርምጃ እንደሚወስዱም ኃላፊነት የተሰጣቸውን መሆኑ ይታወቃል።

ታሪካዊ የተባለው የቡና ወጪ ንግድ ገቢና የቡና ንግድ ብዥታዎች

የአገሪቱ ዋነኛ የውጭ ምንዛሪ ማግኛ በመሆን በቀዳሚነት የሚጠቀሰው ቡና በኢትዮጵያ የቡና ወጪ ንግድ ታሪክ ከፍተኛ የሚባለውን ገቢ ያገኘበት ወቅት መሆኑ ሲገለጥ፣ በአንፃሩ የኢትዮጵያ የቡና ግብይት ላይ ብዥታ የተፈጠረበት ሆኗል፡፡

ከኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለሥልጣን የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው፣ በዘንድሮ ግማሽ ዓመት ከቡና ወጪ ንግድ ከ578 ሚሊዮን ዶላር በላይ ገቢ የተገኘ ሲሆን፣ ይህ ገቢ በግማሽ የበጀት ዓመቱ ይገኛል ተብሎ በዕቅድ ከተያዘውም ሆነ ከቀዳሚው ዓመት ብልጫ ያሳየ ነው፡፡ ይህ የውጭ ምንዛሪ ግኝት በቡና የወጪ ንግድ ታሪክ በግማሽ ዓመት ከግማሽ ቢሊዮን ዶላር በላይ የተገኘበት ትልቁ እንደሆነም መረጃው ያመለክታል፡፡

እንደ ባለሥልጣኑ መረጃ፣ በግማሽ የበጀት ዓመቱ 148,882 ቶን ቡና ለውጭ ገበያ ቀርቦ ለተለያዩ አገሮች ተሸጧል፡፡ ይህ ለውጭ ገበያ የቀረበው ቡና ከቀዳሚው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ሲነፃፀር በ57 ሺሕ ቶን ብልጫ ያለው ነው፡፡

የቡና የወጪ ንግድ እስካሁን በግማሽ ዓመት ከግማሽ ቢሊዮን ዶላር በላይ ገቢ ያስገኘበት ጊዜ የለም፡፡ ኢትዮጵያ ከ25 በመቶ እስከ 30 በመቶውን የውጭ ምንዛሪ የምታገኘው ከቡና ወጪ ንግድ ቢሆንም፣ በየዓመቱ ከምርቱ ይገኛል ተብሎ የሚያዙ ዕቅዶች ሙሉ ለሙሉ አለመሳካታቸውም የሚገለጽ ነበር፡፡

በዘንድሮ ግማሽ ዓመት ግን ከታቀደው ጋር ተስተካካይ የሆነ ገቢ መገኘቱን የሚያመለክቱት የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለሥልጣን የኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ ሳህለማርያም ገብረ መድኅን ለሪፖርተር እንደገለጹት፣ የግማሽ ዓመቱ አፈጻጸም ከዕቅዱ አንፃር እየሄደ ነው፡፡

ባለፉት ሁለትና ሦስት ዓመታት የቡና ወጪ ንግድ የተወሰኑ መሻሻሎች እየታዩበት ቢሆንም፣ ከአንድ ቢሊዮን ዶላር በላይ ለማግኘት ታቅዶ ይህንን ዕቅድ ማሳካት ሳይቻል ቀርቷል፡፡ ዘንድሮ ግን ከቡና የሚገኘው የውጭ ምንዛሪ ግኝት ምናልባትም ከአንድ ቢሊዮን ዶላር በላይ ሊሻገር ይችላል የሚል እምነት አሳድሯል፡፡ ዘንድሮ በግማሽ ዓመት ውስጥ የተገኘው የወጪ ንግድ ግኝትም ጠቋሚ እንደሚሆን ታምኗል፡፡

ዘንድሮ በስድስት ወራት ውስጥ የተመዘገበው ውጤት ምናልባትም በሁለተኛው መንፈቅ ዓመት እንዲሁ ከቀጠለ ኢትዮጵያ በታሪኳ ለመጀመርያ ጊዜ ከቡና ወጪ ንግድ ከአንድ ቢሊዮን ዶላር በላይ የውጭ ምንዛሪ የምታገኝበት ዓመት ሊሆን እንደሚችል ይገመታል፡፡

የስድስት ወራት የቡና ወጪ ንግድ ገቢ ማደግ ዘንድሮ የታየው የዓለም ቡና ዋጋ በመጨመሩ ነው የሚል አመለካከት ስላለ ይህስ አስተዋጽኦ አላደረገም ወይ ለሚለው ጥያቄ፣ ‹‹በዓለም ገበያ የተወሰነ የዋጋ ለውጥ አለ፡፡ እሱም አንድ አስተዋጽኦ አለው፡፡ በጥቅል ሲታይ ግን የሪፎርም ሥራው ትልቅ ለውጥ ማምጣቱ ነው፤›› ብለዋል፡፡

በመንግሥት ዕቅድ መሠረት በ2014 ዓ.ም. በሙሉ በጀት ዓመቱ ኢትዮጵያ ከቡና ወጪ ንግድ ለማግኘት የታቀደው 1.2 ቢሊዮን ዶላር ነው፡፡

በበጀት ዓመቱ የዚህን ያህል የውጭ ምንዛሪ ቡና ሊያስገኝ ከቻለባቸው ምክንያቶች ውስጥ በዓለም አቀፍ ደረጃ የቡና ዋጋ እያደገ መምጣትና የብራዚልና የኮሎቢያ ቡና በውርጭ መመታት ነው፡፡ የባለሥልጣኑ መረጃ ደግሞ፣ ከቡና ምርት ጋር በተያያዘ በተሠራው ሪፎርም ባለፉት ሁለትና ሦስት ዓመታት የቡና ምርት እየጨመረ መምጣቱንም አንድ ምክንያት እንደሆነ ያመለክታል፡፡

ከቨርቲካል ኢንቲግሬሽን ጋር ተያይዞ ማሻሻያዎች ከተደረጉ በኋላ ብዙ ለውጦች እያመጡ ነው ያሉት አቶ ሳህለማርያም፣ ሪፎርሙ የቡና የወጪ ንግድን እንዴት ሊያሳድገው ቻለ? ምን ስለተደረገ? በሚለው ጥያቄ ዙሪያም፣ ‹‹ከዚህ በፊት በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ብቻ ነበር ግብይት የሚፈጸመው፡፡ አሁን የተለያዩ አማራጮች ተፈጥረዋልና እነዚህ የገበያ አማራጮች ጥቅም አስገኝተዋል፤›› ብለዋል፡፡

በዚህ ሪፎርም መሠረት አርሶ አደሩንም በተወሰነ መልኩ ተጠቃሚ እያደረጉት ስለሆነ ምርቱን ቶሎ ቶሎ እያወጣ እንዲሸጥ አስችሏል፡፡ ለምሳሌ ቀደም ሲል በኮንትሮባንክ የሚወጣው ቡና አሁን ላይ አርሶ አደሩም ሆነ ሌላውም ተዋንያን የተሻለ ገቢ ስላገኘበት ወደዚህ ሥርዓት እየገባ በመምጣቱ ውጤቱ መገኘቱን ጠቁመዋል፡፡

ነገር ግን ከሰሞኑ ከቡና ግብይት ጋር በተያያዘ የተፈጠረው ብዥታ አሁን የተገኘውን ዕድል በአግባቡ እንዳንጠቀም እንዳያደርገን መጠንቀቅ አለብን ይላሉ፡፡

በአገር ውስጥ የተሠራው ሪፎርምም ሆነ የዓለም የቡና ዋጋ መጨመርና እንደ ብራዚል ያሉ ዋነኛ ቡና ላኪ አገሮች ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር ተያይዞ በገበያቸው ላይ የገጠማቸው ክፍተት ለኢትዮጵያ መልካም ዕድል የፈጠረ ነው፡፡

በቀጣይ ወራትም የዓለም የቡና ገበያ ዋጋ እየጨመረ ይሄዳል የሚል ትንበያ አለ፡፡ ነገር ግን የኦሮሚያ ክልል ፕሬዚዳንት አቶ ሽመልስ አብዲሳ የኦሮሚያ ቡና አምራቾችና ማኅበራት የቡና ምርታቸውን ለኢትዮጵያ ምርት ገበያ አታቅርቡ ብለዋል ብለው አንዳንድ የቡና አቅራቢዎች እየወሰዱ ያሉት ዕርምጃ ችግር ሊፈጥር ይችላል፡፡

በዚህ ንግግራቸው የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ገበሬዎችንና ማኅበራትን ቡና እየዘረፈ በመሆኑ የበለጠ ተጠቃሚ እንዲሆኑ በቀጥታ ምርታቸውን ለውጭ ገበያ ያቅርቡ የሚል አንደምታ ያለው ነው፡፡ ይህንንም ንግግር ተከትሎ ባለፈው ሳምንትና በአሁኑ ሳምንት ቡናቸውን በኢትዮጵያ ምርት ገበያ በኩል የሚገበያዩ አቅራቢዎች ወደ ምርት ገበያ የሚልኩትን ቡና ቀንሰዋል፡፡

አቶ ሽመልስ የኅብረት ሥራ ማኅበራት ስብሰባ ላይ ተገኝተው የተናገሩት ይህ ንግግር በአሁኑ ወቅት ወደ ኢትዮጵያ ምርት ገበያ የሚቀርበው ቡና እንዲቀንስ አድርጎታል ተብሏል፡፡ ከክልሉ አንዳንድ አቅራቢዎች ወደ ምርት ገበያው የሚያስገቡትን ቡና ያቆሙ ሲሆን፣ ይህም ምርት ገበያው የሚገበያየውን የቡና ምርት መጠን እየቀነሰው መሆኑ ታውቋል፡፡

ከኦሮሚያ ክልል ይቀርብ የነበረው ቡና ወደ ምርት ገበያው አለመግባቱ አጠቃላይ የቡና ግብይት ላይ ችግር ሊፈጥር ይችላል የሚል ሥጋትም አሳድሯል፡፡

አሁንም ምርት ገበያው ከሌሎች ክልሎች የሚመጣውን ቡና እያገበያየ ቢሆንም፣ ከኦሮሚያ ክልል ወደ ምርት ገበያው የሚመጣው መቀነሱን ለማረጋገጥ ችለናል፡፡

ሆኖም የምርት ገበያው በዚህ ጉዳይ ላይ ያለውን አስተያየት ለማወቅ ያደረግነው ጥረት አልተሳካም፡፡ በፌዴራል ደረጃ የወጣውን አሠራር እንዲህ ባለው መልኩ መበረዙ ችግር ሊፈጥር እንደሚችል የሚሠጉ ወገኖች፣ ግብይቱ ሕጋዊ መንገድ ተከትሎ እንዳይጓዝ እንደሚያደርግም ይጠቁማሉ፡፡

ዓለም ባንክ ለምርት ጥራት ማረጋገጫ ፕሮጀክት የሰጠው የ50 ሚሊዮን ዶላር የድጋፍ ጊዜ እንዲራዘም ጥያቄ ቀረበ

ዓለም ባንክ ለምርት ጥራት ማረጋገጫ ፕሮጀክት የሰጠው የ50 ሚሊዮን ዶላር የድጋፍ ጊዜ እንዲራዘም ጥያቄ ቀረበ

በዓለም ባንክ የሚደገፈው የብሔራዊ ጥራት መሠረተ ልማት ፕሮጀክት ትግበራ በሚቀጥለው ሐምሌ ወር የሚጠናቀቅ በመሆኑ፣ የጊዜ ማራዘሚያ መጠየቁን መንግሥት አስታወቀ፡፡

በ2010 ዓ.ም. የተጀመረው ‹‹ብሔራዊ ጥራት መሠረተ ልማት ፕሮጀክት›› ከዓለም ባንክ በተገኘ የ50 ሚሊዮን ዶላር ድጋፍ የሚተገበር ሲሆን፣ በዋናነት ትኩረት አድርጎ የሚያከናውነው በምርት ጥራት ቁጥጥር ላይ የሚሠሩ ተቋማትን መደገፍ ላይ ነው፡፡

ፕሮጀክቱ በተለይም ለኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ፣ ለብሔራዊ ሚትዮሮሎጂ ኤጀንሲ፣ እንዲሁም ለኢትዮጵያ አክሪዲቴሽን ጽሕፈት ቤት የላብራቶሪ መሣሪያዎች ግዥ፣ የሰው ኃይል ሥልጠናና ቴክኒካዊ ድጋፎችን እንደሚያደርግ የፕሮጀክቱ የግል ዘርፍ አስተባባሪ አቶ አባተ አርጋው ገልጸዋል፡፡

ከተመደበው 50 ሚሊዮን ዶላር ውስጥ ለጥራት ፍተሻ የሚሆኑ መሣሪያዎችን ለመግዛት 38 ሚሊዮን ዶላር የተያዘ ሲሆን፣ ቀሪው 12 ሚሊዮን ዶላር ለቴክኒካዊ ድጋፎችና የሰው ኃይል ሥልጠናዎች የሚውል መሆኑን አክለዋል፡፡

እስካሁን 36 ሚሊዮን ዶላር ብቻ መጠቀም እንደተቻለ የገለጹት አቶ አባተ፣ በተለይ የመሣሪያ ግዥ በቀሪው ጊዜ ለማጠናቀቅ ስለማይቻል ቀሪ ሥራዎችን ለማጠናቀቅ የአንድ ዓመት ጊዜ ያስፈልጋል ብለዋል፡፡

ለአምስት ዓመታት እንዲቆይ ታስቦ የተጀመረው ይህ ፕሮጀክት በኮቪድ 19 ወረርሽኝ ምክንያት በውጭ እንዲመረቱ የታዘዙ መሣሪያዎች በጊዜው ተመርተው ባለመምጣታቸው፣ እንዲሁም የሰው ኃይል ሥልጠና ሥራዎች በመጓተታቸው ምክንያት በተመደበው ጊዜ ማጠናቀቅ አለመቻሉን ተናግረዋል፡፡

በዚህም ምክንያት በሐምሌ ወር 2014 ዓ.ም. የሚጠናቀቀውን ይህንን ፕሮጀክት ለአንድ ዓመት እንዲራዘምና ቀሪ ሥራዎች እንዲጠናቀቁ፣ ለዓለም ባንክ ጥያቄ ቀርቧል ብለዋል፡፡

የአዲስ አፍሪካ የንግድ ትርዒትና ኮንቬንሽን ማዕከል የመጀመርያ ምዕራፍ ግንባታ 54 በመቶ መጠናቀቁ ተገለጸ

ከአራት ቢሊዮን ብር በላይ ወጪ ይጠይቃል የተባለው የአዲስ አፍሪካ የንግድ ትርዒትና ኮንቬንሽን ማዕከል የመጀመርያው ምዕራፍ ግንባታ 54 በመቶ መጠናቀቁ ተገለጸ፡፡

በኢትዮጵያ ብቸኛው የንግድ ትርዒትና ተያያዥ አገልግሎቶችን ለመስጠት እየተገነባ ያለው ይህ ማዕከል፣ የመጀመርያው ምዕራፍ ግንባታ በጥቅምት ወር 2010 ዓ.ም. የተጀመረ ሲሆን ሰኔ 2012 ዓ.ም. ይጠናቀቃል ተብሎ ነበር፡፡ ሆኖም በተለያዩ ምክንያቶች ዘግይቶ አሁን ላይ የመጀመርያው ምዕራፍ ግንባታ 54 በመቶ አካባቢ ደርሷል፡፡ በ2014 ዓ.ም. መጨረሻ ላይም የመጀመርያው አጠቃላይ ግንባታ ይጠናቀቃል ተብሎ እንደሚጠበቅ የማኅበሩ ምክትል ሥራ አስኪያጅ አቶ ጋሻው አባተ ገልጸዋል፡፡

በሦስት ምዕራፎች ተከፋፍሎ የሚገነባው ይህ ማዕከል የመጀመርያው ምዕራፍ በቻይናው ‹‹ሲጂሲኦሲ›› በመገንባት ላይ ሲሆን፣ ይህም ከ1.7 ቢሊዮን ብር በላይ ወጪ የሚጠይቅ መሆኑንም ለማወቅ ተችሏል፡፡

ከአክሲዮን ማኅበሩ የተገኘው መረጃ እንደሚያስረዳው፣ የማዕከሉ የመጀመርያ ምዕራፉ ግንባታ ተጠናቅቆ ወደ ሥራ የሚገባበት፣ እንዲሁም የሁለተኛ ምዕራፍ ግንባታ የሚጀምርበት ወቅት ቢሆንም፣ በተያዘው ዕቅድ መሠረት የመጀመርያው ምዕራፍ ግንባታ ማጠናቀቅ አልተቻለም፡፡ ለግንባታው መዘግየት ከአቅም በላይ የሆኑ ጉዳዮች በማጋጠማቸው እንደሆነ የሚያመለክተው የተቋሙ መረጃ፣ በተለይ ግንባታው በተጀመረ በሦስተኛው ወር የብር ምንዛሪ ለውጥ በመደረጉ ከኮንትራክተሩ ጋር ሲደረግ በነበረው ድርድር ጊዜ መወሰዱ፣ ከዚያም በኋላ ኮቪድ-19 ወረርሽኝ መከሰትና የግንባታ ዕቃዎች መወደድ በዋናነት ሊጠቀሱ የሚችሉ ናቸው ተብሏል፡፡

ፕሮጀክቱ ለረዥም ጊዜ ሲያጓትቱ የቆዩ ችግሮች በ2013 ዓ.ም. ይፈታሉ በሚል ዕሳቤ በሒሳብ ዓመቱ ቀሪ ግንባታ የማጠናቀቅ ዕቅድ ተይዞ ነበር፡፡

በጀት ዓመቱ የግንባታ ዕቅድ መነሻ ያደረገው የተቋራጩን የሥራ መርሐ ግብር ሲሆን፣ ሥራ ተቋራጩም በተሰጠው ተጨማሪ ጊዜ ማለትም እስከ ነሐሴ 2013 ዓ.ም. ድረስ ግንባታውን አጠናቆ የማስረከብ ውል ገብቶ ነበር፡፡ በዚሁ መሠረት ከማዕከሉ የመጀመርያ ምዕራፍ አጠቃላይ ግንባታ 57 በመቶ የሆነው በተጠናቀቀው በጀት ዓመት ይከናወናል ተብሎ ይጠበቅ ነበር፡፡

ምንም እንኳን ወደ ማዕከሉ ግንባታ ከተሸጋገረ በኋላ ባጋጠሙት ችግሮች ምክንያት ግንባታውን በተያዘለት ጊዜ ማጠናቀቅ ባይቻልም ፕሮጀክቱን ዳር ለማድረስ የሚደረገው ጥረት አልተቋረጠም፡፡ በመሆኑም እስካሁን ከ600 ቶን በላይ ስቲል ስትራክቸር ወደ አገር ውስጥ ገብቶ በመገጣጠም ላይ የሚገኝ ሲሆን፣ ሌላ 600 ቶን በመርከብ በመጓጓዝ ላይ ይገኛል፡፡

ቀሪው ሁለት ሚሊዮን ቶን ስቲል ስትራክቸር በመመረት ላይ እንደሚገኝም ተጠቅሷል፡፡

እንደ አክሲዮን ማኅበሩ አመራሮች ገለጻ፣ ሁለተኛው የአክሲዮን ሽያጭ ሲጀመር ብዙዎች አክሲዮኑን የመግዛት ፍላጎት ይኖራቸዋል፡፡ ይህም በዚህ ዓመት የመጀመርያው ምዕራፍ ግንባታ ስለሚጠናቀቅና ገቢ ማስገኘት የሚጀምር በመሆኑ ነው፡፡ ብዙዎች ጅምር ሥራውን ዓይተው የሚሳቡ በመሆኑ በበለጠ ይሸጣል የሚል እምነት እንዳላቸው አቶ ጋሻው ሳያመለክቱ አላለፉም፡፡

የማዕከሉ አፍሪካዊ ገጽታንም የያዘ በመሆኑ የአፍሪካውያንን የእርስ በርስ የንግድ ልውውጥ ከማሳደግ አኳያ የራሱ አስተዋጽኦ ይኖረዋል ተብሎ ይታመናል፡፡

አሁን የተጀመረውን ሥራ ማጠናቀቅና ቀጣይ ምዕራፎቹን ሥራ ለማስጀመር ተጨማሪ ገንዘብ የማሰባሰብ ሥራ እንደሚቀጥል ታውቋል፡፡ ተቋሙ ከተፈቀደለት የ1.5 ቢሊዮን ብር ካፒታል ውስጥ ከ1.1 ቢሊዮን በላይ ዋጋ ያለውን የአክሲዮን ሽያጭ ያከናወነ በመሆኑ፣ በመጀመርያው ዙር የተፈቀደለት የካፒታል መጠን ቀሪ አክሲዮን በመሸጥ ሁለተኛ ዙር የአክሲዮን ሽያጭ እንደሚጀምር ታውቋል፡፡

የሁለተኛውን ዙር አክሲዮን ሽያጭ በተለየ ሁኔታ ለመሸጥ ዕቅድ እንዳለውና ትልልቅ ኩባንያዎች በተለይ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች አክሲዮኖችን እንዲገዙ የሚያስችል ሥራ በመሥራት የሚፈለገውን ካፒታል ለማሰባሰብ መታሰቡንም ከተሰጠው ማብራሪያ ለመረዳት ተችሏል፡፡

ይህ ማዕከል ከ20 ዓመታት በፊት በአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት አነሳሽነት የተጠነሰሰ ሲሆን፣ ግንባታውን ለመጀመር ግን ብዙ መንገድ መጓዝ ግድ ብሎታል፡፡

944 የሚሆኑ ባለአክሲዮኖች ያሉት አክሲዮን ኩባንያው፣ እስካሁን ከተከፈለው 1.1 ቢሊዮን ብር ዋጋ ካላቸው አክሲዮኖች ውስጥ 90 በመቶ የሚሆነውን የአክሲዮኑን ድርሻ የያዙት የአዲስ አበባ አስተዳደርና አሥራ አንድ የሚሆኑ መንግሥታዊና የግል ኩባንያዎች ናቸው፡፡

እንደ መረጃው ከሆነ የዚህ ማዕከል ከፍተኛው ባለድርሻ በመሆን የተመዘገበው አዲስ አበባ አስተዳደር እስካሁን በአዲስ አበባ ኤግዚቢሽን ማዕከል ስም 606 ሚሊዮን ብር ዋጋ ያላቸውን አክሲዮኖች የገዛ ሲሆን፣ ከዚህ ሌላ በአስተዳደሩ ሥር ያሉ የተለያዩ ተቋማት ስም ደግሞ 85 ሚሊዮን ብር ዋጋ ያላቸውን አክሲዮኖች በመግዛት በጥቅሉ ከ690 ሚሊዮን ብር በላይ ዋጋ ያላቸውን አክሲዮኖች ማለትም 77 በመቶ ድርሻ ያዟል፡፡

የአክሲዮን ኩባንያው አሥር ሚሊዮንና ከአሥር ሚሊዮን ብር በላይ ዋጋ ያላቸውን አክሲዮኖች ከገዙ አሥራ አንድ የሚሆኑ ኩባንያዎች ውስጥ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ፣ የኢትዮጵያ ጠለፋ መድን ኩባንያ፣ የመንግሥት ማኅበራዊ ዋስትና፣ ዳሽን ባንክ፣ ወጋገን ባንክና የመሳሰሉት ሲጠቀሱ፣ በደቡብ አፍሪካ የሚገኙ ◆ ኢትዮጵያውያን ያቋቋሙት ኢትዮ ሐውስ የተባለ ማኅበር ደግሞ 115 ሚሊዮን ብር ዋጋ ያለው አክሲዮኖች በመግዛት ከአዲስ አበባ አስተዳደር ቀጥሎ የአክሲዮን ማኅበሩ

በአንድ የሒሳብ አካውንት ከአምስት ጊዜ በላይ ገንዘብ ማዘዋወርን የሚከለክለው ገደብ ተነሳ

ገንዘብ እንቅስቃሴን ለመቆጣጠር የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በአንድ የሒሳብ አካውንት በሳምንት ከአምስት ጊዜ በላይ ገንዘብ ማዘዋወር እንደማይቻል የሚደነግገው መመርያን በማሻሻል፣ ገደቡን ማንሳቱን አስታወቀ፡፡ የገንዘብ ዝውውሩን በተመለከተ ቀደም ብሎ የነበረውን ክልከላና ገደብ ያነሳ መሆኑን የሚያመለክተውን መመርያ እንዲተገብሩ መመርያው የተላለፈላቸው ባንኮች፣ ማክሮ ፋይናንሶችና ኢትዮ ቴሌኮም ናቸው፡፡ መመርያውን ባንኮች እንዲያውቁት እና እንዲደርሳቸው እየተደረገ ይገኛል፡፡

ሌላው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የውጭ ምንዛሪ አጠቃቀምና ተቀማጭ ገንዘብን በተመለከተ ያወጣው መመርያ ሲሆን፣ ባንኮች ከሚያገኙት የውጭ ምንዛሪ 70 በመቶውን ለብሔራዊ ባንክ ገቢ ማድረግ እንዳለባቸው ሲያመለክት፣ ላኪዎች በውጭ ምንዛሪ የሚቀመጥላቸው የገንዘብ መጠን ከ40 በመቶ ወደ 20 በመቶ ዝቅ እንዲል አድርጓል፡፡

የወጪ ንግዱ ሥራ የገቢዎችን ተቀማጭ መጠንና አጠቃቀምና አከፋፈልን በተመለከተ በተሻሻለው መመርያ ውስጥ፣ ባንኮች ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ገቢ ማድረግ ያለባቸው የውጭ ምንዛሪ መጠን ወደ 70 በመቶ ከፍ ማለቱን ያሳያል፡፡

እስካሁን ባንኮች ከሚያገኙት የውጭ ምንዛሪ 50 በመቶውን ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ገቢ ሳያደርጉ የነበረ ሲሆን፣ በተሻሻለው መመርያ ግን ይህ ◆ መጠን 70 በመቶ እንዲሆን ተደርጓል፡፡

በዚሁ መመርያ ውስጥ 70 በመቶ ለብሔራዊ ባንክ ገቢ ከተደረገ በኋላ፣ ቀሪው 30 በመቶ ደግሞ ላኪዎችና አገር ውስጥ ተካፋዮች 20 በመቶን በውጭ ምንዛሪ

አስገዳጅ የጥራት ደረጃን ያላሟሉ ምርቶች ወደ ሀገር ውስጥ እንዳይገቡ ታገዱ

በገቢ ምርቶች ላይ በተደረገ የላብራቶሪ እና የኢንስፔክሽን ፍተሻ ከኢትዮጵያ የጥራት ደረጃ በታች የሆኑ ምርቶች ወደ ሀገር ውስጥ ገበያ እንዳይገቡ መታገዳቸውን የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

በተደረገ የላብራቶሪ እና የኢንስፔክሽን ፍተሻ 3 ነጥብ 5 ሜ.ቶ ኤል ኢ.ዲ አምፖል፣ 25 ነጥብ 8 የኤሌክትሪክ ማከፋፈያ፣ 368 ካርቶን ወይም 368 ሺሕ 800 ፍሬ መጠን ያለው የኃይል አባካኝ አንፖል፣ 4 ሺሕ 800 ፍሬ የቤት ክዳን ቆርቆሮ፣ 8.131 ሜ.ቶን የአርማታ ብረት እና 12.6 ሜ.ቶ ጥቅል ቆርቆሮ ወደ ሀገር ውስጥ እንዳይገቡ መደረጋቸው ታውቋል፡፡

በተጨማሪም 5 ሺሕ ፍሬ የፍሎረሰንት አምፖል፣ 293 ካርቶን የኤሌክትሪክ ሶኬት ማከፋፈያ፣ 55.3 ሜ.ቶን የአተር ክክ፣ 24.93 ሜ.ቶ ሩዝ፣ 693.8 ቶን ቀይ ሽንኩርት ወደ ሀገር ውስጥ እንዳይገቡና የኅብረተሰቡን ጤና፣ ደኅንነትና ጥቅም እንዳይጎዱ መደረጉን በሚኒስቴሩ የዘርፉ ዳይሬክተር እያሱ ስምዖን መናገራቸውን የሚኒስቴሩ መረጃ ያመለክታል፡፡

◆

ለተጨማሪ መረጃ፡

ዋና አዘጋጅ፡-
ደበበ አበበ
አዘጋጅ፡-
ዮሴፍ ተሾመ

አድራሻ፡-
ስልክ-፡- +251-115-54-09-93
ፋክስ፡-+251-011-5517699
ድረ-ገጽ፡-
www.ethiopianchamber.com
Facebook:
https://www.facebook.com/
EthiopianChamber
Twitter:
https://twitter.com/
EthiopiaChamber
Telegram:
t.me/ethiopiachamber

ECCSA Resource Center

Ethiopian Chamber of Commerce & Sectoral Associations (ECCSA) Resource Center has stated giving service to member. The center is located at the head quarter of ECCSA.

It is a unit dedicated to serve the business community, its members and staffs with a range of timely and cost-effective information services which will enhance the decision-making process and competitiveness of the chamber system management and the business community.

It is also a WTO (World Trade Organization) Reference Center for the private sector, to enable business community to access online trade data and WTO-related documents on a continuous basis, to help identify market niches for the export of their products and services.

The center works on the principle of the 5Rs: providing the Right information to the Right person at the Right time in the Right quantity and Right quality.

The Center's Services

Reference, Resources Loan & Interlibrary Loan Services

Internet & Electronic Resource Services

Support on information searching

Reprographic Service

Advising users on reference materials available in resource center.

Types of Materials in the Center

Books, Periodicals, Journals, Magazines

Audio and Video CD collections

E-Books & Publications

Business & Economic Statistics & Databases

Access to international organization's online information (WTO, ITC, UNCTAD, World Bank, PACCI, WCO, etc.)

For further information:

Ethiopian Chamber of Commerce and Sectoral Associations

ECCSA Resource & WTO Reference Center

የግልግል አገልግሎት

የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት በማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 341/95 አንቀጽ 5(6) መሰረት በንግድ ማህበረሰቡ መካከል የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን እንዲፈታ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡ በዚህም መሰረት አለመግባባቶችን በፈጣን እና ሚስጥራዊነቱ በተጠበቀ ሁኔታ እንዲፈታ ከማድረጉም በላይ ለባለ ጉዳዮች አመቺ እንዲሆን ቅዳሜንም ጨምሮ ዓመቱን ሙሉ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡ በመሆኑን የዚህ አገልግሎት ተጠቃሚ እንድትሆኑ ስንጠይቅ የንግድ ማኅበረሰቡን ለማገልገል ያለንን ቁርጠኝነት በመግለጽ ነዉ፡፡

ለበለጠ መረጃ ፡- ሜክሲኮ አደባባይ በሚገኘዉ የንግድ ምክር ቤት
ሕንጻ 1ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 15 በአካል በመቅረብ
ወይም
በስልክ ቁጥር +251 115 311015 በመደወል ማነጋገር ትችላላችሁ፡፡

የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት
የግልግል ማዕከል